| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | **የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል፡**<br><br>H - 01<br><br>**46.3 የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ዝርዝር ኘሮፋይል (6 ገፅ)**<br><br>**የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።**<br><br>D - 03 | በአንድ የጨረታ ማስታወቂያ ለወጡት ድርጅቶች ግን ለሁሉም እንዲያገለግል ተመሣሣይ ሆኖ ነው የሚቀረፀው:: በጨረታ ቁጥር 004/87 ለወጡት 11 ፋብሪካዎች የተዘጋጀው መመሪያ አንድ ዓይነት ነው:: በዚህ የተጫራቾች መመሪያ መሠረት:-<br><br>ሀ/ ተጫራቾች በተሰጣቸው መመሪያ እና በቀረቡላቸው ሰነዶች መሠረት የራሳቸውን ጥናትና የዋጋ ትመና ከሠሩ በኋላ በሚሰጡት ግምት መሠረት እስከ 75% ለፈለጉት ድርሻ ያህል ዋጋ እንዲያቀርቡ ይጋብዛል / አንቀፅ 8.1 / :: ከዚህ ውጭ ይኸ ነው የፋብሪካው መነሻ ወይም ጠቋሚ ዋጋ ተብሎ የተገለፀ ነገር እንደሌለ ግልፅ ነው:: ስለሆነም ዐቃቤ ሕግ «<u>በጨረታ ከተገለፀው ጠቋሚ/መነሻ ዋጋ</u>» እያለ ያቀረበው ክስ ሐሰተኛ ነው::<br><br>ለ/ በመመሪያው ገፅ 4 አንቀፅ 8.8 ላይ፣ የፋብሪካው ዋጋ መጨረሻ በሚደረግ የንብረት ቆጠራ መሠረት ማስተካከያ እንደሚደረግበት፣ ተጨማሪ ዕቃ ከተገኘ ከፍ እንደሚል፣ በጨረታ ሰነዱ ከቀረበው ዝርዝር የተቀነሰ ንብረት ከተገኘ ደግሞ ከዋጋው እንደሚቀንስ በግልፅ ተደንግጓል:: ስለዚህ በርክክብ ወቅት የንብረት ቆጠራ ተደርጐ የሂሣብ ማስተካከያ ማድረጉ፣ ገዢ ተጨማሪ ክፍያ እንዲያደርግ መደረጉ ምክንያታዊና ሕጋዊ ሥራ ነበረ:: በደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ላይ በርክክብ ጊዜ በትርፍነት ለተገኙት ጐተራዎች ገዢ ተጨማሪ ገንዘብ እንዲከፍል የተደረገውን ያህል፣ በጣይቱ ሆቴል ላይ ደግሞ ከጨረታ በኋላ በደረሰው ቃጠሎ ንብረቱ በመቀነሱ ከዋጋው ተቀናሽ መደረጉ ትክክልና ሕጋዊ ነው::<br><br>46.3 የፋብሪካው ኘሮፋይል ተሞልቶና ተዘጋጅቶ ለኤጀንሲው የሚላከው በፋብሪካው በተቋቋመ የቴክኒክ ኮሚቴ ነው:: የፋብሪካው የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ የነበሩት የዐቃቤ ሕግ ምሥክር ለፍ/ቤቱ እንዳረጋገጡት ይኸ ኘሮፋይል እሳቸው በሚመሩት ኮሚቴ ተዘጋጅቶ የተላከ ነው:: ከዚህ ሰነድ ማየት እንደሚቻለው፤<br><br>ሀ) ፋብሪካው በ1948 ዓ.ም. በ1 ሚሊዮን ካፒታል የተቋቋመ <u>የስንዴ ዱቄት</u> ፋብሪካ ነበረ:: የማምረት አቅሙም 600 ኩንታል በ24 ሰዓት ነበረ፤<br>ለ) በ1967 ዓ.ም. በደርግ መንግሥት ሲወረስ የነበረው የፋብሪካው ካፒታል ብር 646,936.13 (ስድስት መቶ አርባ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ስድስት ከአስራ ሦስት ሳንቲም) ብቻ ሲሆን የማምረት አቅሙም ወደ 500 ኩንታል ወርዷል:: ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለው ፋብሪካው እያረጀ ሲሄድ <u>በመክሰሩ ካፒታሉንም መብላት ጀምሮ እንደነበረ</u> ነው፤<br><br>ሐ) በዚህ መቀጠል ስላልተቻለ፣ በ1972 ዓ.ም. የድሮው የስንዴ ዱቄት ፋብሪካ ተነቅሎ፣ በምትኩ <u>አዲስ የበቆሎ ወፍጮ</u> እንደተተከለና ለዚህም ብር 4,609,388.94 (አራት ሚሊዮን ስድስ መቶ ዘጠኝ ሺህ ሶስት መቶ ሰማንያ ስምንት ከዘጠና አራት ሣንቲም) በተጨማሪ ኢንቨስት እንደተደረገበት ይነበባል:: የአዲሱ ፋብሪካ ምርቶች <u>የበቆሎ ዱቄትና የበቆሎ ቅንጨ</u> ስለመሆናቸውም በግልፅ ተቀምጧል::<br>መ) በዚህ መልኩ እንደገና የተተከለው የበቆሎ ዱቄት ፋብሪካ፣ በ1987 ዓ.ም. ላይ ለሽያጭ ሲቀርብ ደግሞ በዓመት በአማካይ <u>16 ቀን ብቻ</u> እየሠራ በየዓመቱ በአማካይ ብር 678,135.33 (ስድስት መቶ ሰባ ስምንት ሺህ አንድ መቶ ሰላሳ አምስት ከሰላሳ ሶስት ሣንቲም) እየከሰረ እንደቆየ፣ በዚህም <u>ካፒታሉን በልቶ የጨረሰ ለመሆኑ</u> ተገልጿል:: የመዝገብ ዋጋውም ብር 594,739.03 (አምስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሰባት መቶ |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | | ሰላሳ ዘጠኝ ከሦስት ሣንቲም) ብቻ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡<br><br>ከፍ ብለው ከቀረቡት እውነታዎች፣ የሥራ አመራር ቦርዱ በፋብሪካው ሽያጭ ላይ ሲወያይ፣ ድርጅቱ የከሠረና በመቆም ደረጃ የደረሰ በመሆኑ እስከ መዘጋትና ሠራተኞችም እስከመበተን ድረስ ሊያስከትል እንደሚችል፣ መገመቱ ትክክል ነበረ፡፡ ለሽያጭ የቀረበው ፋብሪካ በእርግጥም የበቆሎ ዱቄት ፋብሪካ እንደሆነ፣ የፋብሪካው የመዝገብ ዋጋም ብር 594,739.03 ብቻ በመሆኑ በ8 ሚሊዮን ብር መሸጡ ጥቅም እንጂ ጉዳት የሌለው ለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡ |
| 47 | የኢትዮጵያ ኘ ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣<br>ቃለ ጉባዔ ቁጥር 11 (8 ገፅ 1 ገፅ አባሪ) ፣<br>የካቲት 29 ቀን 1987 ዓ.ም.<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>D - 04 | 47. በመንግሥት በኩል የዋጋ ትመናም ባይሠራ ድርጅቶቹን ለጨረታ በማቅረብ እንዲሸጡ የሚል ግፊት የነበረ ቢሆንም፣ የሥራ አመራር ቦርዱ ሕጉን ላለመጋፋት ሲል እንዳልተቀበለው (ማስረጃ ተራ ቁጥር 11 ) በሌላ በኩል ግን ኤጀንሲው በራሱ አቅም የዋጋ ትመናውን ሠርቶ ማቅረብ ባለመቻሉ፣ በጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት በኩል ከተለያዩ መ/ቤቶች የተመለመሉ ልዩ ልዩ ባለሙያዎችን አደራጅቶ ሥራውን እንዳስጀመረ አይተናል፡፡<br><br>47.1 በዚሁ መልኩ የተሰባሰቡት ባለሙያዎች መሠረታዊ እውቀቱ ቢኖራቸውም፣ በሕግ የታወቀና የተረጋገጠ የሙያ ብቃት ስለሌላቸው የሥራ ውጤታቸውም እንደዚሁ <u>**ሕጋዊ አስገዳጅነት**</u> ሊኖረው እንደማይችል የተገነዘበው የሥራ አመራር ቦርድ፣ የትመና ሪፖርቱ በኤጀንሲው በኩል በአዋጅ ሕጋዊ ሥልጣኑ ለተሰጠው ለቦርዱ እየቀረበ እንዲፀድቅ በ9ኛ ስብሰባው (ማስረጃ ተራ ቁጥር 32 ) የወሰነውን ያህል፣ በ11ኛ ስብሰባው ደግሞ፡-<br><br>□ ) በእነዚህ ባለሙያዎች ተዘጋጅቶ በሚቀርበው የትመና ሪፖርት መሠረት በጠቋሚ/መነሻ ዋጋነት የሚመረጠው አሃዝ፣ ከገበያው በተጫራቾች በኩል ከሚቀርበው ዋጋ ጋር በማነፃፀር ቦርዱ ውሣኔ እንዲሰጥበት የሚያግዝ <u>ማነፃፀሪያ ወይም reference</u> እንጂ የግድ ከዚህ አሃዝ በላይ ካልሆነ አይሸጥም በሚል መልኩ እንደማይጠቀምበት በቃለ ጉባዔው ገፅ 7 ላይ አስፍሯል፡፡<br>ለ) ከተጫራቾች የሚቀርበው ዋጋ በቦርዱ ግምገማና የጠቋሚ ዋጋ ምርጫ ላይ ተፅዕኖ እንዳያሳድር ለመከላከል እንዲያመቸውም፣ ቦርዱ በዋጋ ትመና ሪፖርቶች ላይ የሚወያየው፣ ተጫራቾች ዋጋዎቻቸውን በሰም በታሸገ ኤንቬሎኘ አሽገው በጨረታ ሣጥኑ ከከተቱ በኋላ ማታውኑ፣ የጨረታ ሣጥኑ ከመከፈቱ በፊት እንደሚሆንም በዚሁ ቃለ ጉባዔ ገፅ 6 ላይ ይነበባል፡፡<br>47.2 ኤጀንሲውን መጀመሪያ ያቋቋመው አዋጅ አንድ ድርጅት ከጠቋሚ/መነሻ ዋጋ እንዳይሸጥ አይከለክልም፣ ይህንን አዋጅ የተካው አዋጅ ቁጥር 146/1991 እንደውም አንድን ድርጅት ከመነሻ ዋጋው መሸጥ እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ የሥራ አመራር ቦርዱ ገና ምንም ዓይነት የሽያጭ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት በዚሁ ጉዳይ ላይ ተወያይቶ፣ የመነሻ/ጠቋሚ ዋጋ ተብሎ የሚመርጠው አሃዝ በጨረታ ከሚገኘው ዋጋ ጋር በማነፃፀር ለውሣኔው እንዲያግዘው እንጂ ከዚሁ አሃዝ በታች እንዳይሸጥ የሚከለክለው እንደማይሆን ግልፅ አቋም ይዞበታል፡፡ ይኸ አቋሙ ለኤጀንሲው መመሪያ እንደሚሆንም በቃለ ጉባዔው አስፍሮታል፡፡ በዚህ አንፃር፡-<br>ሀ) የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ በአማላካች ዋጋነት ከተያዘው አሃዝ ዝቅ ባለ ዋጋ በመሸጡ ሕግ ወይም መመሪያ እንደተጣሰ ተደርጐ የቀረበው ክስም መሠረት የሌለው ለመሆኑ ግልፅ ነው፤ በተመሣሣይ መልኩ ነትራዎቹን በተመለከተ ቦርዱ የሰጠው ውሣኔም ህጋዊና ትክክለኛ ስለመሆኑ ያስረዳል፤ |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
| --- | --- | --- |
| | | [illegible]) በአንፃሩ ደግሞ ከጠቋሚ ዋጋ በታች እንዲሸጥ የተደረገው ደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ብቻ ባለመሆኑ፤<br>ይኸ ክስ አድልዎ ሣይፈፀም አድልዎ ተፈፀመ በሚል ለምንና በምን መሥፈርት እንደቀረበ ለመረዳትም መንገድ ይከፍታል። |
| 48 | የኢትዮጵያ ፕ ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣ቃለ ጉባዔ ቁጥር 14 (7 ገፅ)፣<br>መጋቢት 21 ቀን 1987 ዓ.ም.<br><br>**የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።**<br><br>D - 05 | 48. ይህ 14ኛው የቦርድ ቃለ ጉባዔ፣ <u>የቦርድ ውሣኔዎች ተግባራዊ ከመሆናቸው በፊት በበላይ አካል</u> ስለመፅደቃቸው እንደዚሁም <u>ከአመላካች ዋጋ በታች ስለመሸጥ</u> መቻል፣ የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች ያስረዳል።<br>48.1 የመጀመሪያው አዋጅ ቁጥር 87/1986፣ በድርጅቶች ሽያጭ የመጨረሻውን ውሣኔ የሚሰጠው ማን እንደሆነ በግልፅ አያስቀምጥም። የኤጀንሲው ተጠሪነት ለጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት እንደሆነ ግን በአዋጁ በግልፅ ተቀምጧል። የሕጉ ጉዳይ እንዲህ ከመሆኑ በተጨማሪ ኤጀንሲው ገና አዲስና በተሟላ መልኩ ያልተደራጀም በመሆኑ፣ አብዛኛው ሥራ ሲካሄድ የነበረው ከጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት በሚሰጠው የሰው ኃይልና የማቴሪያል ድጋፍ እንደዚሁም <u>ቀጥተኛ አመራርና ውሣኔ መሠረት ነው።</u><br><br>ሀ) ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት በመንግሥት በተሰጠው መመሪያ መሠረት፣ ማንኛ ውም ሽያጭ <u>የሚፀድቀውና ተግባራዊ የሚሆነው፣ በጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት ተገምግሞ የመጨረሻው የይሁንታ ውሣኔ ሲያገኝ ብቻ ነበረ።</u> የሥራ አመራር ቦርዱ ይህንን መመሪያ በቀጥታ ለኤጀንሲው ያስተላለፈ ለመሆኑ በዚሁ ቃለ ጉባዔው ገፅ 5 ላይ «**ከፍ ብሎ የቀረቡት የሽያጭ ውሣኔዎች**» ተግባራዊ ከመሆናቸው በፊት «**ለበላይ እንዲቀርቡና እንዲፀድቁ**» ሲል መመሪያ ሰጥቶበታል።<br>ለ) ከመጀመሪያዎቹ የ1987 ዓ.ም. ጨረታዎች ጀምሮ እስከ 1993 ዓ.ም. የተደረጉት ሽያጮች በሙሉ ተግባራዊ የሆኑት ከፍ ብሎ በተቀመጠው መልኩ ለጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት እየቀረቡ የመጨረሻው ውሣኔ በዚሁ አካል ከተሰጠባቸው በኋላ ነው። እስከ 1988 ዓ.ም. ድረስ ለተፈፀሙት ሽያጮች፣ <u>ሐረር ማተሚያ ቤትንና ደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካን ጨምሮ</u>፣ ጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት የሰጣቸውን የመጨረሻ ውሣኔዎች <u>በፅሑፍ ለኤጀንሲው</u> ያስተላለፈ ሲሆን፣ ከዚያ በኋላ ግን <u>ይሁንታውን በቃል ነበር የሰጠው።</u><br>ሐ) የሥራ አመራር ቦርድ፣ ከሽያጭ ውሣኔ በፊት ስላሉት የዝግጅትና የጨረታ ሂደቶች ብቻ ሳይሆን፣ የሽያጭ ውሣኔው ስለሚሰጥበትና ተፈፃሚ ስለሚሆንበት ሁኔታው ግልፅ መመሪያ አስቀምጦ ነው ሥራውን የጀመረው። እያንዳንዱ የሽያጭ ውሣኔ ተግባራዊ የሆነውም ኤጀንሲው የውሣኔ ሃሣብ ከቀረበበት በኋላ ቦርድ አቋም እየወሰደበትና፣ ይህ የቦርዱ አቋም ለመንግሥት ቀርቦ ተቀባይነት ማግኘቱ ከተረጋገጠ በኋላ ለመሆኑ ግልፅ ነው። በዚህ ሁኔታ <u>መንግሥት ሳያውቀው በ1ኛ ተከሳሽ ትእዛዝና ውሣኔ የተፈፀመ ሽያጭ እንዳለ</u> በማስመሰል የቀረበው ክስ አሳፋሪ ቅጥፈት ብቻ ነው ሊባል የሚችለው።<br><br>48.2 በዋጋ ትመናው ውጤት መሠረት የሚገኘው አሃዝ ለማነፃፀሪያነት እንጂ ከዚህ አሃዝ በላይ ካልሆነ ድርጅቱ አይሸጥም በሚል መልኩ እንደማይጠቀምበት ቦርድ ቀደም ብሎ አቋም ስለመያዙ በማስረጃ ተራ ቁጥር 47 ላይ አይተናል። በዚህ መሠረት የመጀመሪያዎቹ ጨረታዎች ተከፍተው ከተገመገሙ በኋላ ሪፖርቱ ለቦርድ ቀርቦ ወይይት እንደተደረገበትና አሃዞችን እያነፃፀረ ቦርዱ የመጀመሪያውን ሽያጭ እንደፈቀደ በዚሁ ቃለ ጉባዔ ይነበባል። የተጫራቾች ዋጋ ከትመናው ውጤት ጋር ሲነፃፀር ከፍ ወይም ዝቅ ማለቱ አንድ መመዘኛ ሆኖ የታየ ቢሆንም፣ ለሽያጭ ውሣኔ የግድ የጨረታ ዋጋ ከተመኑ መብለጥ አለበት በሚል መልኩ የተቀመጠ ነገር የለም። |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | | |
| 49 | የኢትዮጵያ ኘ ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 20 (10 ገፅና 1 ገፅ አባሪ) ፣ ሰኔ 19 ቀን 1987 ዓ.ም.<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>D - 06 | 49. ይህ ሃያኛው የሥራ አመራር ቦርድ ቃለጉባዔ የሚከተለውን ያስረዳል፡-<br>49.1 በዚህ ቃለ ጉባዔ እንደሚነበበው የሥራ አመራር ቦርዱ ከተወያየባቸው ነጥቦች አንዱ ሐረር ማተሚያ ቤትንና ደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካን ጨምሮ በጨረታ ቁጥር 004/87 ስለወጡት 11 ፋብሪካዎች የዋጋ ትመና ነበረ። የፋብሪካዎችን ዋጋ ለመተመን ኤጀንሲው የተጠቀመባቸውን ዘዴዎች፣ የወሰዳቸውን ታሳቢዎችና ያገኛቸውን ውጤቶች በሪፖርት መልክ የቃለ ጉባዔው ቀርቦ ውይይት እንደተደረገበት ከመገለፁ በተጨማሪ ውጤቱም በሠንጠረዥ መልክ የቃለ ጉባዔው አባሪ ሆኖ ተያይዞ ቀርቧል። ከዚሁ መረዳት እንደሚቻለው፤<br>ሀ) ፋብሪካዎቹ ለጨረታ የቀረቡት የካቲት 1987 ላይ ቢሆንም የዋጋ ትመና ሪፖርቱ ተጠናቅቆ ለቦርዱ ውሣኔ የቀረበው ግን ሰኔ 19 ቀን 1987 ዓ.ም. ለተደረገው 20ኛ የቦርድ ስብሰባ ነው። ስለሆነም በጨረታ ሰነድ ሊገለፅ የሚችል ጠቋሚ ዋጋ ጨረታው በወጣበት ወቅት ስላልነበረ፣ አልተገለፀም። ዐቃቤ ሕግ እንደነበረ አድርጐ ያቀረበው ክስ ሐሰትና መሠረተ ቢስ ነው።<br>ለ) ተገቢ መረጃዎችን በማሰባሰብ የኤጀንሲው ባለሙያዎች ካለምንም ተፅዕኖ ወይም Bias ተገቢ የመሰላቸውን ተመን ለ11 ፋብሪካዎች ሠርተው ለቦርዱ አቅርበዋል፣ ቦርዱም በተመሣሣይ መልኩ ተወያይቶ የመሰለውን ወሣኔ ሰጥቷል። ይህ ውሣኔ ሲሰጥ ጨረታው ተዘጋ እንጂ ገና ያልተከፈተ በመሆኑ፣ ለየትኛው ፋብሪካ ምን ያህል ተጫራች እንደቀረበ፣ ማን እንዳቀረበ፣ ምን ዓይነት ዋጋ እንዳቀረበ፣ ወይም ደግሞ ከእነጭራሹ ተጫራች ስለመቅረብ አለመቅረቡም የሚታወቅ ነገር ስላልነበረ፣ ውሣኔው በእውነትም ነፃና ከተፅዕኖ ውጭ ለመሆኑ አያጠራጥርም።<br>ሐ) በዚሁ መሠረት ለሐረር ማተሚያ ቤት በገቢ ዘዴ ተሠርተው ሦስት አማራጭ አሃዞች ቀርበው ቦርዱ አንዱን መርጧል፣ ለደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ደግሞ በመተኪያ ዘዴ አንድ፣ በገቢ ዘዴ ደግሞ ሦስት አማራጮች በድምሩ አራት አማራጮች ቀርበውለት ቦርዱ በመተኪያ ዘዴ የተሠራውን ተቀብሏል። የቦርዱ ምርጫ ከተፅዕኖ ነፃ ሆኖ የየፋብሪካውን ሁኔታ ግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ የተወሰነ ለመሆኑ ግልፅ ነው።<br>መ) በመተኪያ ዘዴ የሚሠራው የዋጋ ትመና የሚያተኩረው «ንብረቱን አሁን ለመተካት የሚያስፈልገው ዋጋ» ምን ያህል እንደሆነ በማስላት ላይ ነው። የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ጠቋሚ ዋጋ እንዲሆን የተመረጠው አሃዝ የተገኘው ደግሞ በመተኪያ ዘዴ ከተሠራው ተመን እንደሆነ በቃለ ጉባዔውና አባሪ ሆኖ በተያያዘው ሠንጠረዥ ተገልጿል። ሀቁ ይኸው ሆኖ እያለ፣ ዐቃቤ ሕግ ባቀረበው ክሱ ላይ የደብረዘይት ዱቄት ጠቋሚ ዋጋ የተተመነው በገቢ ዘዴ ነበረ፤ በሚል የቀረቡት አባባሎች በሙሉ ሐሰትና መሠረተ ቢስ ለመሆናቸው ግልፅ ሆኗል።<br>ሠ) የዋጋ ትመናውን ሪፖርት ገምግሞ ውሣኔ የሰጠው የሥራ አመራር ቦርዱ ነው፣ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ጨረታው ተከፍቶ ውጤቱ ከማነፃፀሪያ አሃዞቹ ጋር ተገናዝቦ እንዲቀርብለት ውሣኔ የሰጠውም ይኸው ቦርድ ነው። ከዚህ ውጭ 1ኛ ተከሳሽ የሰጡት ውሣኔ የለም። ቦርዱ በእዚህ ጉዳይ ላይ እንዲወስን ደግሞ በአዋጅ ሥልጣኑም ሆነ ሃላፊነቱ ተሰጥቶታል። ስለዚህ 1ኛ ተከሳሽ የሰጡት ውሣኔ በማስመሰል እና ውሣኔውም ሕገወጥ እንደሆነ በማስመሰል የቀረበው ክስ መሠረት የሌለው ለመሆኑ ግልፅ ነው።<br><br>49.2 ይህ ቃለ ጉባዔ የትመና ውጤት ከጨረታ ውጤት ጋር ሲነፃፀር ለቦርዱ የሽያጭ ውሣኔ |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | | ስለነበረው እንደምታም የሚያስረዳው ሀቅ አለ፡፡ በማስረጃ ተራ ቁጥር 47 (ቃለ ጉባዔ ቁጥር 11) ላይ እንደተገለፀው፣ የትመና ውጤት በጨረታ የተገኘውን ዋጋ ለመገምገም እንደማነፃፀሪያነት ያገለግላል እንጂ ከዚያ በላይ ካልሆነ አይሸጥም ለሚል ዓይነት ውሣኔ እንደማያገለግል ቦርዱ ቀደም ብሎ አቋም ወስዶበታል፡፡ በዚሁ መሠረት በጨረታ ቁጥር 003/87 ላይ ለወጡት ሆቴሎች የተሠራውን የዋጋ ትመና ሪፖርት ባየበት 19ኛ የቦርድ ስብሰባ ላይ «ከቀረቡት ስምንት አማራጮች የተሻሉ ሆነው ያገኛቸውን ሦስት አማራጮች መርጦ የቀረቡት የጨረታ ዋጋዎች ከእነዚህ ሦስት አማራጮች ጋር <u>ተነፃፅረውና ተገምግመው</u> እንዲቀርቡ መመሪያ ሰጥቶ» እንደነበረ በ20ኛ ቃለ ጉባዔ ገፅ 3 ላይ ተዘግቧል፡፡ እዚህ ላይ በግልፅ እንደሚነበበው ቦርድ ለማነፃፀሪያነት የሚሆነውንም አሃዝ በአማራጭ እንዲታዩ ሦስቱን መረጠ እንጂ አንድ ብቻ አለመሆኑን ነው፡፡ ኤጀንሲውም በተሰጠው መመሪያ መሠረት፡-<br><br>ሀ) ለጨረታ ከቀረቡት ሆቴሎች ውስጥ ለስድስቱ ሆቴሎች የቀረበለትን የገበያ ዋጋ ከሦስቱ አማራጭ ተመኖች ጋር አነፃፅሮ፣ ለውሣኔ ለቦርዱ እንዳቀረበ (ገፅ 4)<br>ለ) ቦርዱም አሃዞችን ሲያነፃፅር፣ «የትኛው አማራጭ ነው ለገበያው ዋጋ የተሻለ ምላሽ የሰጠው?» በሚል መመዘኛ ዙሪያ አማራጮችን ገምግሞ «በአማራጭ አንድ 6 ሆቴሎች ወይም ጨረታ ከቀረበላቸው 14 ሆቴሎች 43% ያህሉን መሸጥ ይቻላል፡፡ ይህ በአማራጭ አንድ የተተመነው መነሻ ዋጋ ከገበያው ጋር የተቀራረበ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ስለሆነም የሥራ አመራር ቦርዱ ሽያጩ በዚህ አማራጭ መሠረት እንዲፈፀም ወስኗል፡፡» በማለት በገፅ 5 ላይ ተዘግቧል፡፡<br>▯ ) ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው፣ ቦርዱ የትመና አሃዞችን የተጠቀመው ትመናው ከገበያው ጋር ያለውን ርቀትና ቅርበት ለመለካትና ለማነፃፀር አንደሆነና በዚሁ መሠረትም ከሦስቱ አማራጮች አነስተኛውን አሃዝ የሰጠውን አማራጭ በመውሰድ ስድስቱ ሆቴሎች እንዲሸጡ ስለመወሰኑ ነው፡፡ ይህ ውሣኔ ለመንግሥት ቀርቦ ስለፀደቀ ሽያጩም ተፈፃሚ ሆኗል፡፡<br><br>መ) ይህ ሽያጭ የተፈፀመው ከደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ሽያጭ በፊት በመሆኑ፣ ቦርዱ ከያዘው ማነፃፀሪያ ዋጋ በታች የተሸጠው <u>ደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ብቻ እንደሆነ፣ ከእሱ በፊትም ሆነ በኋላ የዚህ ዓይነት ሽያጭ እንዳልተፈፀመ</u>፣ በዚህም አድልዎ እንደተፈፀመ መስሎ የቀረበው ክስ ሐሰተኛ ለመሆኑ ያረጋግጣል፡፡<br><br>49.3 በዚሁ ቃለ ጉባዔ ገፅ 2 ላይ እንደሚነበበው፣ ኤጀንሲው ከየካቲት 1987 ዓ.ም. እስከ ሰኔ 1987 ዓ.ም. ያደረገው እንቅስቃሴ ለመንግሥት ሪፖርት ቀርቦበት ተገምግሟል፡፡ በአጠቃላይ ውጤቱ እንደተጠበቀው አለመሆኑ የተገለፀ ሲሆን በምክንያትነት ከተጠቀሱት በርካታ ጉዳዮች ውስጥ <u>«የልማት ድርጅቶችን በአነስተኛ ዋጋ ላለመሸጥ ከሚገባው በላይ ጥንቃቄ መውሰድና ዋጋዎችን ከፍ አድርጐ የመተመን ዝንባሌ መታየት»</u> ዋነኛው እንዲሆን ተገልጿል፡፡ ይህ ነጥብ ኤጀንሲው በተደጋጋሚ የተገመገመበትና የተወቀሰበት ከመሆኑ አንፃር ዐቃቤ ሕግ የኤጀንሲውን የዋጋ ትመና እንደገና በማሠራት ያውም ከአሥር ዓመት በኋላ ውጤቱ አነስተኛ ነበረ ለማለት መሞከሩ እንደምታውና ዓላማው ክፉ ለመሆኑ ያመላክታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይኸው ሀቅ፤<br><br>▯ ) የኤጀንሲው እንቅስቃሴ በየወቅቱ ለመንግሥት ሪፖርት እየቀረበበት እየተገመገመና እየተሻሻለ የቀጠለ፣ ካለመንግሥት እውቅናና ፈቃድ የተሠራ አንድም ነገር እንደሌለ ያስረዳል፤ |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | | ለ) መንግሥት ሂደቱን ገምግሞ በዋጋ ትመና ሥርዓቱ ላይ ብቻ ሣይሆን፣ በጨረታ ሰነዶቹ ላይ መነሻ/ጠቋሚ ዋጋ አለመገለፁም ችግር እንደፈጠረና «ወደፊት በሚወጡት ጨረታዎች የመሸጫ መነሻ ዋጋ በጨረታ ሰነዶቹ ውስጥ ሊገለፅ የሚችልበት ሁኔታ» እንዲታይ እንደተባለም ተገልጿል:: ስለሆነም በመጀመሪያው ዙር በ1987 ዓ.ም. በወጡት ጨረታዎች ላይ መነሻ/ጠቋሚ ዋጋ የተገለፀ በማስመሰል የቀረበው ክስ ሐሰት መሆኑን ያስረዳል:: |
| 50 | የኢትዮጵያ ኘ ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣<br>ቃለ ጉባዔ ቁጥር 21 (5 ገፅና 1 ገፅ አባሪ) ፣<br>ሰኔ 26 ቀን 1987 ዓ.ም.<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>D - 07 | 50. የሥራ አመራር ቦርድ በ21ኛው ስብሰባ ላይ የተወያየው በአብዛኛው በጨረታ ቁጥር 004/87 ለወጡት ፋብሪካዎች በቀረበው የጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴ ሪፖርት ላይ ነው:: የሥራ አመራር ቦርዱ በ20ኛው ስበሰባው ላይ ባስቀመጣቸው የጨረታ ጠቋሚ ዋጋዎች አንፃር ጨረታው ተከፍቶ እንዲገመገም ባዘዘው መሠረት፣ ኤጀንሲው የግምገማ ሪፖርቱን ከውሣኔ ሃሣብ ጋር ይዞ ቀርቧል:: በዚህ ላይ ቦርዱ ካደረገው ውይይትና ከሰጣቸው ውሣኔዎች የሚከተሉትን መረዳት ይቻላል::<br>50.1 በአንድ ጨረታ ላይ ከቀረቡት 11 ፋብሪካዎች ውስጥ ተጫራቾች የቀረቡት ለአምስት ፋብሪካዎች ብቻ ስለመሆኑ፣ ከእነዚህ ውስጥ ቀደም ሲል በቦርድ የተሰጠውን የዋጋ ማነፃፀሪያ አሃዝ መሠረት በማድረግ በተደረገ ግምገማ፤<br>ሀ) ለአድዋ ዱቄት ፋብሪካና ለሐረር ማተሚያ ድርጅት የቀረበው የገበያ ዋጋ ከማነፃፀሪያ ተመኑ የሚሻል በመሆኑ ሽያጩ እንዲቀጥል፤<br>ለ) ለደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ የቀረበው የገበያ ዋጋ ከማነፃፀሪያ ተመኑ በ7.75% የሚያንስ ቢሆንም ፋብሪካው የከሰረና ሊዘጋ በሚችልበት ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ሽያጩ እንዲቀጥል፤<br>ሐ) በተመሣሣይ መልኩ ለትግራይ ዱቄት ፋብሪካ የቀረበው ጨረታ ከማነፃፀሪያ ተመኑ በ37% ያህል ያነሰ ቢሆንም ይህ ፋብሪካም የመዘጋት አደጋ ያንዣበበት በመሆኑ እንዲሸጥ፤<br>ሲል የሥራ አመራር ቦርድ በሙሉ ድምፅ ወስኗል:: ይህንን ውሳኔ የሰጡት 1ኛ ተከሳሽ ብቻ ሳይሆኑ ፤<br>• አቶ አሰፋ አብርሃ<br>• አቶ ጀነነው አየለ<br>• አቶ ሐጎስ ደበሱ<br>• ዶ/ር ተገኘወርቅ ጌጡና<br>• አቶ በሻህ አዝምቴን ያካተተው ቦርድ ለመሆኑ ግልፅ ነው።<br>ይህ የቦርዱ አቋም የጠ/ሚ/ር ጽ/ቤትም ተቀብሎት ሽያጩ እንዲቀጥል መመሪያ ስለሰጠበት (ማስረጃ ተ/ቁ. 53) ውሣኔው ተግባራዊ ሆኗል:: እዚህም ላይ ግልፅ እየሆነ ያለው፣ የድርጅቶቹ ሽያጭ የተወሰነው በ1ኛ ተከሳሽ ትእዛዝ አለመሆኑ ብቻ ሣይሆን ከማነፃፀሪያ ተመን በታች የተሸጠው ድርጅት ደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ብቻ ባለመሆኑ አድሎአዊ የሚባልበት ምክንያት የሌለ መሆኑን ነው::<br>50.2 ከፍ ብሎ ከቀረበው በተጨማሪ የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ የሚያመርተው የበቆሎ ዱቄት ስለመሆኑ፣ ምርቱ በገበያ የማይፈለግ በመሆኑ በሥራ ላይ የሚውለው የማምረት አቅሙ 2.5% ብቻ ለመሆኑ፣ ለተከታታይ ዓመታት የከሰረና አደገኛ ሁኔታ ላይ የደረሰ ለመሆኑ በጨረታ ሰነዱ ላይም የተቀመጠ ሃቅና ቦርዱም ለውሣኔው እንደመነሻ የተጠቀመበት ለመሆኑ በቃለ ጉባዔው ይነበባል::<br>50.3 በጨረታ ሰነድ ላይ ጠቋሚ/መነሻ ዋጋ ይገለፅ የሚል ሃሣብ ከበላይ አካልም በተሰጠው |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፣ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | | መሠረት (ማስረጃ ተ.ቁ. 49 )፣ ተግባራዊ እንዲሆን ውሣኔ የተሰጠውም በዚሁ ቃለ ጉባዔ ለመሆኑ በገፅ 4 ላይ ይነበባል:: |
| 51 | የኢትዮጵያ ኘ ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣<br>ቃለ ጉባዔ ቁጥር 19 ( 7 ገፅ)፣ ግንቦት 30 ቀን 1987 ዓ.ም.<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>D - 08 | 51. በ17ኛውና በ18ኛው የቦርዱ ስብሰባዎች በተከታታይ ውይይት የተደረገበት የሆቴሎች የዋጋ ትመና ጥናት መቋጫ ያገኘው በ19ኛው የቦርዱ ስብስባ ላይ ነበረ:: ቦርዱ በዚህ ስብሰባው ላይ በሆቴሎች ሥራ አስኪያጆች በኩል ተሠርተው የቀረቡ አራት አማራጮችንና በኤጀንሲው የተዘጋጁ አራት አማራጭ የትመና ውጤቶችን በዝርዝር መርምሯል:: ይሁን እንጂ ከእነዚህ ስምንት አማራጮች ውስጥ አንዱን መምረጥ ስላስቸገረው ሦስቱን አማራጮች ነበር የተቀበለው:: በዚህ መሠረትም ጨረታዎቹ ተከፍተው የቀረቡት የገበያ ዋጋዎች በእነዚህ ሦስት አማራጭ የትመና ዘዴዎች ከሚገኙት ማነፃፀሪያ አሃዞች አንፃር ተገምግመው እንዲቀርቡለት መመሪያ የሰጠ ለመሆኑ ገፅ 15 ላይ ይነበባል:: በተሰጠው መመሪያ መሠረት ተሠርቶ በቀረበው ንፅፅር ላይ ተወያይቶ አነስተኛውን ማነፃፀሪያ አሃዝ መሠረት አድርጐ ብዙ ሆቴሎች ለመሸጥ የሚያስችለውን አማራጭ እንደተቀበለና በዚህ መሠረት እንደወሰነ ደግሞ ማስረጃ ቁጥር 49 ሆኖ በቀረበው 20ኛ የቦርዱ ቃለ ጉባዔ ላይ ይታያል:: ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለው:-<br><br>ሀ) የኤጀንሲው ሥራ አመራር ቦርድ በሚቀርቡለት የዋጋ ትመና ሪፖርቶች ላይ በዝርዝር ተወያይቶ ተገቢ የመሰለውን ውጤት እንደሚቀበል፤<br>ለ) ይህ የትመና ውጤት የሚጠቀምበት ለማነፃፀሪያነት በመሆኑ፣ አንድ ብቻ ሣይሆን ሁለትና ሦስት ማነፃፀሪያ አሃዞችን ይዞ ጨረታዎች እንዲገመገሙ ካደረገ በኋላ ተገቢ የመሰለውን ውሣኔ እንደሚሰጥ፤<br>ሐ) ቦርዱ ከያዘው ማነፃፀሪያ አሃዝ በታች እንዳይሸጥ የሚከለክለው ሕግ ያለመኖሩን ያህል፣ እንዲህ ዓይነት ውሣኔ የተሰጠውም በደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ላይ ብቻ አለመሆኑን፤<br>መ) ስለሆነም አድልዎ ተፈፀመ፣ ልዩ ነገር ተሠራ ወዘተ. በሚል የቀረበው ክስ መሠረት የሌለው መሆኑን፣<br>ነው:: |
| 52 | የኢትዮጵያ ኘ ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ በደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ዋጋ ተመንና ሺያጭ ላይ ውሣኔ የሰጠባቸው ቃለ ጉባዔዎች ቁጥር 20 እና 21 በወቅቱ ለጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት የተላኩ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ደብዳቤ፤ /1 ገፅ/<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ | 52. የኤጀንሲው ተጠሪነት ለጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት ስለመሆኑ በአዋጁ በግልፅ ተደንግጓል:: የኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ አባላት፣ የኤጀንሲው ሥራ አስኪያጅና የሥራ ሃላፊዎች፣ እንደዚሁም ፀሃፊዎችና ባለሙያዎች በሙሉ የተመደቡት በዚሁ ጽ/ቤት ከመሆኑ በተጨማሪ ኤጀንሲው ስለኘሮግራሙ አፈፃፀምና ዕቅድም በቀዳሚነት ሪፖርቱን የሚያቀርበው ለዚሁ ጽ/ቤት ነው:: ከዚሁ በተጨማሪ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ሆነው ከ1986 እስከ 1987 ድረስ ያገለገሉት አቶ ተከስተብርሃን ገ/ሚካኤልም ሆነ ከ1987 እስከ 1993 ያገለገሉት አቶ አሰፋ አብርሃ በጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት የኢኮኖሚ ዘርፍ፣ እንደቅደም ተከተላቸው ሃላፊና አባል ሆነው የሠሩ ነበሩ:: በተለይ ከ1988 ዓ.ም. ጀምሮ የኤጀንሲው የቦርድ አባላት ሆነው የሰሩት እነ አቶ ተፈራ ዋልዋ፣ ዶ/ር ከበደ ታደሰ፣ አቶ መስፍን ለማ፤ አቶ ሙሉጌታ ዓለምሰገድና አቶ ቢተው በላይ በጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት በተለያዩ ዘርፎች በሃላፊነት የሚሠሩ ነበሩ:: አቶ ማሕተመ ሰለሞንና አቶ ሱፍያን አህመድ ደግሞ የካቢኔ አባል ሚኒስትሮች ነበሩ:: እነዚህ የኤጀንሲው ሃላፊዎችና የቦርድ አባላት ለጽ/ቤቱ ከሚያቀርቡት የቃልና የፅሑፍ ሪፖርት በተጨማሪ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ቃለ ጉባዔዎች በበቂ ኮፒ ተባዝተውና ተፈርሞባቸው ከሽኚ ደብዳቤ ጋር ለጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት በየወቅቱ ይላካሉ:: ከዚህ ሁሉ በመነሳት:-<br>ሀ) የጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት እንደአካል፣ እንደዚሁም ጠ/ሚኒስትሩና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሃላፊዎች በሙሉ በሂደቱ በቀጥታ የተሳተፉና ስለእያንዳንዱ ሽያጭ በዝርዝር እያወቁ |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>D – 09 | መመሪያና ውሣኔ ሲሰጡ የነበሩ ስለመሆኑ ግልፅ ነው::<br><br>ለ) ከ1987 ዓ.ም. እስከ 1988 ዓ.ም. ለተፈፀሙት ሽያጮት በሙሉ፣ የኤጀንሲው ሥራ አመራር ቦርድ ያቀረባቸውን ሃሣቦች ከቃለ ጉባዔውና ከመግለጫዎቹ ከገመገመ በኋላ ጽ/ቤቱ የመጨረሻ ውሣኔዎቹን በፅሑፍ ለኤጀንሲው ያሳወቀ ሲሆን፣ የድሮው ቦርድ ፈርሶ ከፍ ብለው የተጠቀሱት ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት በቦርድ አባልነት ከተመደቡበት ከ1988 ዓ.ም. በኋላ ደግሞ ውሣኔውን በም/ጠ/ሚ/ር በኩል በቃል እያረጋገጠ ነው ሽያጭ የተፈፀመው::<br><br>[illegible]) በዚህ አንፃር መንግሥት ሳያውቅ ወይም ሳይፈቅድ የተሸጠ ድርጅት እና የተፈፀመ ሽያጭ ያለ በማስመሰል በተለይም ደግሞ የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ከተያዘለት ጠቋሚ ዋጋ በታች የተሸጠው መንግስት ሳያውቅ በማስመሰል የቀረበው የዐቃቤ ሕ[illegible] ክስ መሠረት የሌለው ነገር ስለመሆኑ ግልፅ ነው:: |
| 53 | ደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካና ሐረር ማተሚያ ቤትን ጨምሮ ለተሸጡት አራት ድርጅቶች ሐምሌ 6 ቀን 1987 ዓ.ም. ከጠ/ሚ/ር ፅ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ (1 ገፅ)<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>B - 28 | 53. ኤጀንሲው በሚያቀርባቸው ሪፖርቶች፣ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢና አባላት በሚያቀርቡዋቸው መግለጫዎችና በቦርዱ ቃለ ጉባዔዎች በኩል በሚያገኘው መረጃ፣ መንግሥት ስለፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራሙ ሂደት በቂ ዕውቀት የነበረው ስለመሆኑ ከፍ ብሎ ቀርቧል:: የማንኛውም ድርጅት ሽያጭ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ለጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት ቀርቦ መፅደቅ እንዳለበት በተሰጠው መመሪያ መሠረት የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ሽያጭም ለመንግስት ቀርቦ ፀድቋል።<br>[illegible]) ድርጅ[illegible] የተሸጠው በ1ኛ ተከሳሽ ትእዛዝና ውሣኔ ሳይሆን፣ ጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት በሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ በመሆኑ፣ 1ኛ ተከሳሽን ሃላፊ ለማድረግ የሞከረው የዐቃቤ ሕግ ክስ መሠረተ ቢስ ነው:: ጥፋት የለም እንጂ ኖሮ እንኳን ቢሆን 1ኛ ተከሳሽን አይመለከትም::<br>[illegible]) ውሣኔ ከተሰጠባቸው ድርጅቶች ውስጥ ደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ጨምሮ አንዳንዶቹ የተሸጡት ከኤጀንሲው የዋጋ ተመን ባነሰ ዋጋ ስለመሆኑ፣ በቃለጉባዔው በግልፅ የተቀመጠ በመሆኑ መንግሥት ውሣኔውን የሰጠው ይህንንም እያወቀ ነበረ:: ከዚህ አንፃር የቀረበው የዐቃቤ ሕግ ክስ የሕግ ድጋፍ የሌለው ከመሆኑ በተጨማሪ ውሣኔውን የሰጠው አካል እያወቀ ለማይመለከተው አካል ያቀረበው ስለመሆኑ ግልፅ ነው:: |
| 54 | የኢትዮጵያ ፕ ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣<br>ቃለ ጉባዔ ቁጥር 23 (5 ገፅ )፣<br>ነሐሴ 19 ቀን 1987 ዓ.ም.<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br>H - 05 | 54. ይህ 23ኛ የቦርድ ቃለ ጉባዔ የሚከተለውን ፍሬ ነገር ያስረዳል::<br><br>ቦርዱ ከዚሁ ቀደም ብሎ በ14ኛው ስበሰባው ላይ፣ የቦርዱ ውሣኔዎች ተግባራዊ የሚሆኑት ለበላይ አካል ቀርበው ከፀደቁ ብቻ ስለመሆኑ ለኤጀንሲው መመሪያ የሰጠ ስለመሆኑም በማስረጃ ተራ ቁጥር 48 ቀርቧል:: በዚህ መመሪያ መሠረት የጠ/ሚኒስትሩ ልዩ ጽ/ቤት የቦርዱ ውሣኔ ተቀባይነት ያገኘ በመሆኑ፣ የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ፤ የሐረር ማተሚያ ቤትና ሌሎች ድርጅቶች ሽያጭ እንዲቀጥል የፅሑፍ መመሪያ የሰጠ ስለመሆኑ፣ አሁን በቀረበው 23ኛ የቦርዱ ቃለጉባዔ ተዘግቧል:: በዚህ ቃለ ጉባዔ ከተጠቀሱት ደብዳቤዎች ውስጥ በማስረጃ ተራ ቁጥር 53 የተጠቀሰው አንዱ እንደሆነ ቁጥሩና ቀኑ ያረጋግጣል:: |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| 55 | በመንግሥት ይዞታ ሥር እንዲቆይ ተደርጐ የነበረው የፋብሪካዎቹ 25% ድርሻ አብዛኛውን ድርሻ 75% ለገዙት ባለሀብቶች እንዲሸጥ የሚያዝና ጥቅምት 21 ቀን 1988 ዓ.ም. ከጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት ለኤጀንሲው የተላከ ደብዳቤ (1 ገፅ)<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>B - 31 | 55. ከ1984 ዓ.ም. ጀምሮ ሀገሪቱን ሲመራ የነበረው በጠ/ሚ/ር ታምራት ላይኔ የሚመራው የሽግግር መንግሥት ሥልጣኑ አብቅቶ፣ በ1988 ዓ.ም. አዲስና በጠ/ሚ/ር መለስ ዜናዊ የሚመራው መንግሥት ተቋቋመ:: አዲሱ ካቢኔ ተሰይሞ አዲሱ የጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት አመራር የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራሙን እንደገመገመና በዚሁ መሠረትም መመሪያዎችና ውሣኔዎችን እንደሰጠ በማስረጃ ተራ ቁጥር 18 ላይ አይተናል:: ከእነዚህ ውሣኔዎች ውስጥ የ□ረር ማተሚያ ቤትና የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካን ሽያጭ በተመለከተ ቀደም ሲል ሐምሌ 6 ቀን 1987 ዓ.ም. የፅሑፍ ትእዛዝ የተሰጠበት ስለሆነ ተጨማሪ ደብዳቤ መፃፍ አላስፈለገም:: የሥራ አመራር ቦርድን ስለማጠናከር የተሰጠው ውሣኔም ከፍ ብሎ በማስረጃ ተራ ቁጥር 20 እና 21 እንደተጠቀሰው ተፈፃሚ ሆኗል:: በተመሣሣይ መልኩ መመሪያ ተሰጥቶበት የነበረው የ25% ድርሻ ጉዳይም በዚህ ደብዳቤ ውሳኔው በፅሑፍ ለኤጀንሲው ደርሶታል:: በመሆኑም ከዚህ ደብዳቤ የሚከተለውን መረዳት ይቻላል::<br><br>□) ደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካንና ሐረር ማተሚያ ቤትን ጨምሮ በ1987 ዓ.ም. ወደ ግል ይዞታ ከተዛወሩት ፋብሪካዎች ውስጥ የድርሻቸውን 25% በመንግሥት ይዞታ ሥር እንዲቆይ ተደርጐ የነበረ ቢሆንም፣ ይኸ አሠራር ተሽሮ ይህ የፋብሪካዎቹ ቀሪ 25% ድርሻ፣ 75% ድርሻውን ለገዙት ባለሀብቶች እንዲሸጥ መንግሥት የወሰነ መሆኑን፣ እና<br>□) በዚህ መሠረትም፣ ይህንን ውሣኔ የሠጡት 1ኛ ተከሳሽ እንደሆኑ በማስመሰል የቀረበው የዐቃቤ ሕግ ክስ መሠረተ ቢስ ሐሰት ስለመሆኑ፣ ያስረዳል፤<br>□) ይህን የመንግሥት ውሣኔ የሚከለክልና ሕገወጥ የሚያሰኝ ምንም ዓይነት ሕግ የሌለ ከመሆኑ በተጨማሪ ውሣኔው የተሰጠው በሁሉም ሽያጮች ላይ እንጂ አንዱን ሽያጭ ከሌላኛው በተለየ በሚመለከት መልኩ ባለመሆኑ አድሎአዊ የሚባልበት ምክንያት የለም::<br>□) ስለሆነም ሕገወጥ ውሣኔ ወይም አድሎአዊ ውሣኔ እንደተሰጠ በማስመሰል የቀረበው የዐቃቤ ሕግ ክስም ሐሰትና መሠረተ ቢስ ነው:: |
| 56 | መስከረም 4 ቀን 1999 ዓ.ም ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካን በሚመለከት የተሰጠ ማረጋገጫ /1 ገፅ/<br><br>ዋናው በተከሳሾች እጅ ይገኛል ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>D - 10 | 56. ቀደም ሲል የመንግሥት የልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣንና የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በሚል ይታወቁ የነበሩት ሁለት የተለያዩ አካላት ከሐምሌ 26 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 412/ 1996 መሠረት ተዋህደው አንድ አካል ሆነዋል።<br>ይህ መ/ቤት የደብረዘይት የዱቄት ፋብሪካን በተመለከተ በሰጠው የፅሁፍ ማረጋገጫ፤<br>ሀ/ የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ለሽያጭ ሲቀርብ በወጡት የመጀመሪያዎቹ የ1987 ዓ.ም ጨረታዎች ላይ በኤጀንሲው ተሠርቶ ለተጫራቾች የተገለፀ ጠቋሚ ወይም መነሻ ዋጋ ያልነበረ መሆኑን፤<br>ለ/ ይልቁንስ ተጫራቾች የየራሳቸውን ዋጋ ይዘው እንዲቀርቡ የተጋበዙ መሆኑን፤<br>ሐ/ በሂደቱ ኤጀንሲውም ለራሱ የውስጥ ፍጆታ የሚጠቀምበት የዋጋ ትመና አሠርቶ ለማነፃፀሪያነት የሚጠቀምበት አሃዝ ያዘጋጀ መሆኑን፤<br>መ/ በመጨረሻም የጨረታ ዋጋዎችን ከኤጀንሲው ተመን ጋር በማነፃፀር ውሣኔ መስጠቱንና<br>ሠ/ የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካን ጨምሮ በርካታ ድርጅቶች ከተያዘላቸው ጠቋሚ/መነሻ ዋጋ በታች እንዲሸጡ የተወሰነ መሆኑን፤<br>ያስረዳል። በዚህም አንድን ድርጅት ከተያዘለት ጠቋሚ ዋጋ በታች መሸጥ የተለመደና በህግም ይሁን በመመሪያ ያልተከለከለ አሠራር መሆኑን አረጋግጧል። |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| 57 | <u>**ጠቋሚ ዋጋ ሳይገለፅ ወይም ደግሞ ከተገለፀው ጠቋሚ ዋጋ በታች እንዲሸጥ መወሰን፣ ጥፋት ሳለመሆኑና አድሎአዊ የሚባልም ሳለመሆኑ የሚያስረዱ ማስረጃዎች**</u><br>**በዚህ ስር የተጠቀሱት ሰነዶች፤ የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።** | **57. ዐቃቤ ሕግ በክሱ ላይ በተደጋጋሚ ያነሳውና አድልዎ እንደተፈፀመ አድርጎ የሚጠቅሰው ጉዳይ የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ከጠቋሚ ዋጋ በታች ተሸጠ የሚለው ነው:: በደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ጨረታ ላይ የተገለፀ አሃዝ እንዳልነበረ፣ እንደዚሁም አንድን ድርጅት ከጠቋሚ ዋጋ መሸጥ የሚከለክል ሕግ እንደሌለ፣ እንዳውም አዋጅ ቁጥር 146/1991 ሊሸጥ እንደሚችል ታሣቢ አድርጎ እንደሚነሳ ወዘተ. ከዚህ በፊት ባቀረብናቸው ማስረጃዎቻችን አስረድተናል:: ጠቋሚ ዋጋ ሳይገለፅለት ወይም ደግሞ ከጠቋሚ ዋጋ በታች የተሸጠ ድርጅት ደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ብቻ ስላለመሆኑና ሌሎች በርካታ ድርጅቶችም በዚሁ መንገድ የተሸጡ ስለመሆናቸውም በተደጋጋሚ አሳይተናል:: ከዚህ በተጨማሪ፣ የሚከተሉት ሰነዶች፣ ከደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ በፊት፣ ደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ በተሸጠበት ወቅትና ከተሸጠም በኋላ በበርካታ ድርጅቶች ሽያጭ ላይ ተመሣሣይ ውሣኔ የተሰጠ መሆኑን ያስረዳሉ::** |
| | **57.1 የኢትዮጵያ ኘራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 13 (5 ገፅ)፣ መጋቢት 7 ቀን 1987 ዓ.ም.**<br>D - 11 | **57.1 የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ለጨረታ ከመቅረቡ በፊት በጨረታ ቁጥር 001/87 እና 002/87 ለሽያጭ የቀረቡት መጋዘኖች ዋጋ ትመና ሣይሠራላቸውና በጨረታ ሰነድ ላይ የተገለፀ ጠቋሚ ዋጋ ሳይኖራቸው ነበር ለጨረታ የቀረቡት:: ሁለቱም ጨረታዎች መጋቢት 7 ቀን 1987 ዓ.ም ከተዘጉ በኋላ፣ በቀረበለት የዋጋ ትመና ጥናት ላይ የተወያየው የሥራ አመራር ቦርድ፣ ለማነፃፀሪያነት የሚሆን ቁርጥ ያለ አሃዝ ሳይሆን በታሣቢዎችና በአማራጮች ላይ ተወያይቶ፣ በመረጣቸው አማራጮች መሠረት ከሚገኘው አሃዝ ጋር ንፅፅር ተደርጎ ውጤቱ እንዲቀርብለት መመሪያ እንደሰጠ በዚሁ ዕለት የተያዘው ቃለ ጉባዔ ቁጥር 13 ያስረዳል:: በሦስት አማራጮች ተሠርተው የተገኙትን ሦስት አሃዞች፣ በነጋታው መጋቢት 8/1987 ጨረታው ሲከፈት ከተገኙት የተጫራቾች ዋጋዎች ጋር በማነፃፀር ተሠርቶ፣ በቀረበለት ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ቦርዱ የሽያጭ ወሣኔ የሰጠ ለመሆኑ ማስረጃ ተ.ቁ. 48 ሆኖ በቀረበው ቃለ ጉባዔ ቁጥር 14 ላይ ይታያል::** |
| | **57.2 የኢትዮጵያ ኘራይቬይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመ ራር ቦርድ ስብሰባ፣ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 48 (11 ገፅ)፣እና ቃለ ጉባኤ ቁ.** 49 /9 **ገፅ** /<br>D – 12 እና D - 13 | **57.2 ለለገደንቢ የወርቅ ማዕድን በጨረታ ሰነድ ተገልጾ የተቀመጠው ጠቋሚ ዋጋ 185 ሚሊዮን ዶላር ለመሆኑ ቃለጉባዔ ቁጥር 48 ያስረዳል::** በቃለ ጉባኤ 48 ገፅ 4 ላይ እንደተነበበው የቀረበው ትልቁ ዋጋ 172 ሚልዮን ዶላር ሆኖ፤ ድርጅቱ በዚሁ ዋጋ እንዲሸጥ ስለመወሰኑ ደግሞ **ቃለ ጉባዔ ቁጥር 49 ያስረዳል::** |
| | **57.3 የኢትዮጵያ ኘራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣ቃለ ጉባዔ ቁጥር 25 (12 ገፅ)፣ መስከረም 9 ቀን 1988 ዓ.ም.**<br>B - 30 | **57.3 በቃለ ጉባዔው ገፅ 5 ጀምሮ እንደሚነበበው በማስታወቂያ ቁጥር 001/87 ለሽያጭ ለቀረቡት የለስላሳ መጠጥ ፋብሪካዎች፣ በማስታወቂያ ቁጥር 002/87 ለሽያጭ ለቀረቡት የግዮን ሆቴልና ዋቢ ሸበሌ ሆቴሎች ሰንሰለቶች፣ እንደዚሁም በማስታወቂያ ቁጥር 003/87 ለሽያጭ ለቀረቡት አግሮ ኢንዱስትሪዎች፣ ኤጀንሲው በነበረው የአቅም ውሱንነት ምክንያት የዋጋ ትመና ማሠራት አለመቻሉን፣ ይሁን እንጂ የግድ ለጨረታ መቅረብ ስለነበረባቸው የጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት ልዩ ግብረሃይል አቋቁሞ ዋጋቸውንና የቀረበላቸውን ጨረታ ካስገመገመ በኋላ ወሣኔ እንደሰጠባቸው ተዘግቧል:: በዚሁ መሠረትም ቦርዱ ተወያይቶ ውሣኔውን ለማስፈፀም እንደተስማማ ይነበባል:: ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው::**<br><br>**ሀ) የዋጋ ትመና ሣይሠራለት ወይም ጠቋሚ ዋጋ ሳይገለፅለት ለጨረታ የቀረበ ድርጅት ደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ብቻ እንደሆነ ተደርጎ የቀረበው ክስ ሐሰት ነው::** |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | | ▯) ከደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ጨረታ በፊትና ከዚሁ ፋብሪካ ጋር ለጨረታ ቀርበው በተመሣሣይ መንገድ የተሸጡ ድርጅቶች የመኖራቸውን ያህል <u>**አሠራሩ መንግሥትም ያወቀውና የተቀበለው**</u> ለመሆኑ ግልፅ ነው::<br><br>▯) ስለሆነም ሕግ እንደተጣሰ፣ አድልዎ እንደተፈፀመ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ 1ኛ ተከሳሽን እንደሚያስጠይቅ ተደርጎ የቀረበው የዐቃቤ ሕግ ክስ መሠረተ ቢስ ለመሆኑ ያስረዳል:: |
| | 57.4 የኢትዮጵያ ኘራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 55 (8 ገፅ)፣ ጥቅምት 12 ቀን 1990 ዓ.ም<br>D – 14 | 57.4 ለአዶላ ወርቅ ማዕድን፣ የተቀመጠው ጠቋሚ ዋጋ 21.04 ሚሊዮን ዶላር ለመሆኑ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 49 (ማስረጃ ተ.ቁ. 57.2 ) ገፅ 14 ላይ ያስረዳል፣ የተሸጠው ግን በ15 ሚሊዮን ዶላር ለመሆኑ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 55 ያስረዳል:: |
| | 57.5 የኢትዮጵያ ኘራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 50 (5 ገፅ) እና ቃ/ ጉባኤ ቁጥር 59 / 5 ገፅ/<br>D . 15 እና D .16 | 57.5 የተተመነለት ጠቋሚ ዋጋ 18.591 ሚሊዮን ዶላር የነበረው የጐጃም-ጐንደር እርሻ ልማት ድርጅት፣ በ12.4 ሚሊዮን ዶላር እንዲሸጥ ስለመወሰኑ ቃለጉባዔ ቁጥር 59 ገፅ 16 ላይና ቃለ ጉባኤ ቁጥር 105 ገፅ 6 ላይ ያስረዳል:: |
| | 57.6 የኢትዮጵያ ኘራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 57 ( 9 ገፅ)፣ ታህሳስ 8 ቀን 1990 ዓ.ም.<br>D – 17 | 57.6 በተመሣሣይ መልኩ በቃለ ጉባዔ ቁጥር 55 /ማ.ተ.ቁ 57.4/፣ የጠቋሚ ዋጋው ብር 194,806,422.00 (አንድ መቶ ዘጠና አራት ሚሊዮን ስምንት መቶ ስድስት ሺ አራት መቶ ሃያ ሁለት) እንዲሆን ተወስኖ የነበረው የመካከለኛ አዋሽ እርሻ ልማት ድርጅት፣ በብር 177,632,000.00 (አንድ መቶ ሰባ ሰባት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺ) እንዲሸጥ የተወሰነ ለመሆኑ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 57 ገፅ 6 ላይ ያስረዳል:: |
| | 57.7 የኢትዮጵያ ኘራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 105 ( 4 ገፅ)፣ ግንቦት 2 ቀን 1992 ዓ.ም.<br>D – 18 | 57.7 በቃለ ጉባዔ ቁጥር 57 ገፅ 11 /ማ.ተ.ቁ.57.6/ ላይ 38,958,435.00 (ሰላሳ ስምንት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ስምንት ሺ አራት መቶ ሰላሳ አምስት) ዶላር ተተምኖ የነበረው የቀንቲቻ ማዕድን ልማት፣ በ25 ሚሊዮን ዶላር እንዲሸጥ ስለመወሰኑ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 105 ገፅ 5 ላይ ያስረዳል:: |
| | 57.8 የኢትዮጵያ ▯ራይቬታይዘሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 112 ( 5 ገፅ)፣ ነሐሴ 3 ቀን 1992 ዓ.ም.<br>D – 19 | 57.8 በቃለ ጉባዔ ቁጥር 112 ላይ የተዘረዘሩት የከብት እርባታ እርሻዎች በሙሉ የተሸጡት ከተያዘላቸው ጠቋሚ ዋጋ በታች ለመሆኑ ቃለ ጉባዔው ያስረዳል:: በተለይ ደግሞ ብር 10,098,000.00 የተገመተው ቀቃ የከብት እርባታ በብር 6,500,000.00 እንደተሸጠ፤ ብር 3,819,000.00 የተገመተው ሞጆ ከብት እርባታ በብር 2,681,000.00 እንደተሸጠ፤ ብር 1,499,000.00 የተገመተው አልሜ ከብት እርባታ በብር 1,200,000.00 እንደተሸጠና ብር 1,669,000.00 የተገመተው ሰላሌ ከብት እርባታ ደግሞ በብር 1,200,000.00 እንደተሸጠ በገፅ 3 ና 4 ላይ ተዘግቧል።<br><br>57.9 በብር 3,895,194.00 (ሦስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና አራት) የተተመነው የአሳማ እርባታ ድርጅት በብር 1,800,260.00 (አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ ሁለት መቶ ስድሳ) እንደተሸጠ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 74 ▯▯ 11 ▯▯ 12 ▯▯ ያስረዳል:: በብር 1,149,713.00 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | **57.9 የኢትዮጵያ ን ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 74 ( 3 ገፅ)፣ እና ቃለ ጉባኤ ቁጥር** 89 / 5 ገፅ/<br>D - 20 እና D - 21 | አስራ ሶስት) ተተምኖ የነበረው የጅማ የከብት እርባታ ደግሞ በብር 800,000.00 (ስምንት መቶ ሺህ) የተሸጠ ለመሆኑ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 89 ገፅ 3 እና 4 ላይ ያስረዳል::<br>57.10 በ1989 ዓ.ም. ለሽያጭ የቀረቡት የአርሲ እርሻ ልማት ድርጅት፣ የባሌ እርሻ ልማት ድርጅት እና የወለጋ እርሻ ልማት ድርጅት፣ ጠቋሚ ወይም መነሻ ዋጋ ሳይገለፅላቸው ለጨረታ እንዳቀረቡ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 50 / ማስረጃ ተ.ቁ 57.5 / ያስረዳል:: በተመሣሣይ መልኩ ከፍ ብለው የተጠቀሱት የጐጃም-ጐንደር እርሻ፣ መካከለኛ አዋሽ እርሻ፣ ቀንቲቻ ማዕድን፣ እንደዚሁም ድሬደዋ ሲሚንቶ ፋብሪካና ቅዱስ ጊዮርጊስ ቢራ ፋብሪካ ለጨረታ ሲቀርቡ በጨረታ ሰነድ ላይ የተገለፀላቸው ዋጋ አልነበረም::<br>57.11 ለማሣያ ያህል እነዚህን ጠቀስን እንጂ፣ በተመሣሣይ መንገድ ጠቋሚ ወይም መነሻ ዋጋ ሳይቀመጥላቸው፣ ተቀምጦም ከሆነ ከዚሁ ዋጋ በታች እንዲሸጡ ውሣኔ የተሰጠባቸው፣ ድርጅቶች በጣም ብዙ ናቸው:: ይህ አሠራር የተፈቀደ እና በበርካታ ሽያጭ ላይ ተግባራዊ የሆነ ስለመሆኑ የዐቃቤ ሕግ ምሥክሮች ሆነው የቀረቡት የኤጀንሲው ባለሙያዎችና ሃላፊዎችም በተደጋጋሚ ያረጋገጡት ጉዳይ ነው:: |

## 5. [illegible]

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| 58 | ሰኔ 4 ቀን 1989 ዓ.ም በቁጥር ደዘምኢ/ህ/ወ/ 023 /89 ከህራየር ቤሄስኒ.ሊ.ያንና ቤተሰቡ ለኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ የተፃፈ ደብዳቤ / 4 ገፅ/<br>ዋናው አቤቱታ አቅራቢው ዘንድ የሚገኝ፣ ፎቶ ኮፒ ቀርቧል።<br>D — 22 | 58. የኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ የጎተራዎችን ጉዳይ በመረመረበት ወቅት የተወያየበት ሰነድ ይህ የገዢው የይግባኝ ማመልከቻ ብቻ ነበር። ጉዳዩ በይግባኝ ላይ የመወሰን እንጂ፤ በዋጋ ትመና ላይ የመወሰን ባለመሆኑ፤ ከኤጀንሲው በኩል ቀርቦለት የተወያየበትና ያፀደቀው " በባለሙያ የተሠራ" የሚባል ተመን አልነበረም። ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው፤<br>ሀ/ ብር 3.407. 708.40 የሚለው አሃዝ ገዢና ኤጀንሲ በጉዳዩ ዙሪያ ሲፃፃፉ፤ ኤጀንሲው የጠቀሰው አሃዝ እንጂ፤ በባለሙያ ተሠርቶ ለቦርዱ የቀረበና ያፀደቀው ዋጋ አይደለም።<br>ለ/ በዚህ ማመልከቻ ውስጥ በገዢ በኩል የተጠቀሰው ዋጋ ብር 547,402.73 ብቻ ነው፤ ከዚህ ውጭ የቀረበ ስለሌለ፤ በብይኑ ላይ ቦርድ ያፀደቀው በገዢ በኩል የቀረበለትን አሃዝ እንደነበረ ሆኖ የቀረበው ስህተት ነው። ቦርዱ ያፀደቀው ብር 2,041,104.86 የሚለው አሃዝ፤ በውይይቱ ወቅት፤ በኤጀንሲው በኩል ከቀረበ መረጃ የተገኘ ነበረ።<br>ሐ/ ከማመልከቻው መረዳት እንደሚቻለው፤ በጨረታ ሰነዱ ላይ ተጠቅሰው የነበሩ ሆኖም ግን ኤጀንሲው ሊያስረክባቸው ያልቻሉ 10 ሌዝ ማሽኖችም እንደነበሩ፤ ግምት ውስጥ ገብቷል።<br>መ/ ጎተራዎቹ ለ13 ዓመታት በፀሃይና ዝናብ ላይ የተቀመጡ ስለመሆናቸው፤ የጎደሉ ዕቃዎች እንደነበሯቸው፤ የኤጀንሲው ስሌት የተጋነነ እንደሆነ፤ ወዘተ ማመልከቻውም የገለፃቸው ቦርዱም በውይይቱ ወቅት ግምት ውስጥ ያስገባቸው ጉዳዮች ነበሩ። |
| 59 | የኢትዮጵያ ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጁ ቁጥር 87/1986 (4 ገፅ)<br>ፎቶ ኮፒ ቀርቧል።<br>B - 03 | 59. ይህ አዋጅ የካቲት 10 ቀን 1986 ዓ.ም. ወጥቶ ኤጀንሲውን ለመጀመሪያ ጊዜ ያቋቋመው አዋጅ ነው:: በ1991 ዓ.ም. በወጣው አዋጅ ቁጥር 146/1991 እስከተተካበት እስከ <u>ታህሣስ 20 ቀን 1991</u> ዓ.ም. ድረስ የነበረው የኤጀንሲው እንቅስቃሴ የተመራውም በዚህ አዋጅ መሠረት ነበረ:: በአጠቃላይ ይህ አዋጅ በሥራ ላይ በነበረበት ዘመን የነበረውን የኤጀንሲው እንቅስቃሴ በተለይ ደግሞ በዚሁ ወቅት ውሣኔ የተሰጠበትን <u>የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ፣</u> በሚመለከት፣ አዋጁ የሚከተለውን ያስረዳል::<br>59.1 የኤጀንሲውን አቋም በሚደነግገው አንቀፅ 6 ሥር ኤጀንሲው፣ የሥራ አመራር ቦርድ፣ ዋና ሥራ አስኪያጅ እና አስፈላጊ ሠራተኞች እንደሚኖሩት ተገልጿል:: ይሁን እንጂ <u>«የሥራ አመራር ቦርድ ሊቀመንበር</u>» የሚባልና ራሱን የቻለ ሥልጣን፣ ሃላፊነትና ተግባራት ያሉት |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | | አካልን አላቋቋመም:: የቦርዱ ስብሰባ በሚለው አንቀፅ 9 ሥር ከተገለፀው የስብሰባ ሥርዓትን የሚመለከት ድንጋጌ ውጭ የቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ሊቀመንበር እንደቃል እንኳ የተጠቀሰበት ቦታ የትም የለም:: በዚህ አንፃር:-<br><br>▯/ ዐቃቤ ሕግ የቦርድ ሊቀመንበሩን የተለየ ሥልጣንና ተጠያቂነት ያለው በማስመሰል መክሰሱ አግባብነት የለውም::<br><br>▯/ የሥራ አመራር ቦርዱ በጋራ ለወሰነው ውሣኔ የቦርዱ ሰብሳቢ ብቻ ሃላፊና ተጠያቂ የሚሆንበት ሕጋዊ መሠረትም የለም::<br><br>59.2 በጨረታ የተገኘው ዋጋ ከጠቋሚ ዋጋ በታች ከሆነ ሽያጭ እንዳይፈፀም የሚከለክል ድንጋጌ የለም:: ስለዚህ ከጠቋሚ ዋጋ በታች ሽያጭ ተፈፀመ፣ በማለት በዐቃቤ ሕግ ክስ ላይ የተነሳው መሠረተ ቢስ ነው::<br><br>59.3 በአንቀፅ 8 /5/ መሠረት ቦርዱ በኤጀንሲው ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡለትን ይግባኞች መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥ ሃላፊነት ተጥሎበታል። ከደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ጋር በተያያዘ በተለይ ጎተራዎቹን በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ ህጋዊ መሆኑም ያረጋግጣል። |
| 60 | በጨረታ ቁጥር 004 / 87 ለደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ፤ የተጫራቾች መመሪያ (8 ገፅ)<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>H - 01 | 60. የተጫራቾች መመሪያ ተብሎ የቀረበው ሰነድ ከጨረታ፣ ጨረታ የተወሰነ ልዩነት ቢኖረውም በአንድ የጨረታ ማስታወቂያ ለወጡት ድርጅቶች ግን ለሁሉም እንዲያገለግል ተመሣሣይ ሆኖ ነው የሚቀረፀው:: በጨረታ ቁጥር 004/87 ለወጡት 11 ፋብሪካዎች የተዘጋጀው መመሪያ አንድ ዓይነት ነው:: በመመሪያው ገፅ 4 አንቀፅ 8.8 ላይ፣ የፋብሪካው ዋጋ መጨረሻ በሚደረግ የንብረት ቆጠራ መሠረት ማስተካከያ እንደሚደረግበት፣ ተጨማሪ ዕቃ ከተገኘ ከፍ እንደሚል፣ በጨረታ ሰነዱ ከቀረበው ዝርዝር የተቀነሰ ንብረት ከተገኘ ደግሞ ከዋጋው እንደሚቀንስ በግልፅ ተደንግጓል:: ስለዚህ በርክክብ ወቅት የንብረት ቆጠራ ተደርጐ የሂሣብ ማስተካከያ ማድረጉ፣ ገዢ ተጨማሪ ክፍያ እንዲያደርግ መደረጉ ምክንያታዊና ሕጋዊ ሥራ ነበረ:: በደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ላይ በርክክብ ጊዜ በትርፍነት ለተገኙት ጐተራዎች ገዢ ተጨማሪ ገንዘብ እንዲከፍል የተደረገው ትክክልና ሕጋዊ ነው:: |
| 61 | ጥር 3 ቀን 1988 ዓ.ም በኤጀንሲውንና በሀራያር ቤሄስኒልያንና ቤተሰቡ መካከል የተፈረመው የሽያጭ ውል / 4 ገፅ /<br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br>D - 23 | 61. ይህ ውል፤ ሺያጩን የፈቀደው የጠ/ሚ/ር ፅ/ቤት ስለመሆኑ ከማረጋገጡ በተጨማሪ፤ የፋብሪካው የመጨረሻ ዋጋ የሚወሰነው በቆጠራ ወቅት በሚገኘው የንብረት ዝርዝር መሠረት የመጨረሻ ማስተካከያ ከተሠራ በኋላ ስለመሆኑም ያስረዳል። |
| 62 | <u>ስለደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ዳግም የዋጋ ትመና፣</u> | 62. ኤጀንሲው የሠራው የመጀመሪያው የዋጋ ትመና ጥናት የተመሠረተው ከፋብሪካው በቀረቡለት መረጃዎች ላይ ነበረ:: ይሁን እንጂ በሂደት በተለይ ከፋብሪካው ሥራ አመራር ጋር በተደረገው ውይይት ላይ አንዳንድ የመረጃ ለውጦች እንደተነሱም በመገመት፣ ጥናቱ እንደገና |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | 62.1 ጥር 1 ቀን 1988 ዓ.ም. የቀረበው የኤጀንሲው የዳግም ትመና ሪፖርት<br>(5 ገፅ)<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>D - 24<br><br>62.2 የፌደራል ዋና ኦር መ/ቤት፤ የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካን ዋጋ እንዲተምን ያሠማራው ቡድን፤ ሕዳር 1996 ዓ.ም አዘጋጅቶ ለፍ/ቤቱ ያቀረበው ሪፖርት፤ / የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ሆኖ ቀርቦ ከነበረው፤ በከፊል የቀረበ፤ /6 ገፅ እና 1 ገፅ አባሪ/<br><br>ዋናው በፍ/ቤቱ የሚገኝ ኮፒ ቀርቧል።<br>D – 25 | እንዲመረመር ተደርጓል፡፡<br>62.1 የፋብሪካው የመጨረሻ ርክክብ ከመደረጉ በፊት ጥር 1 ቀን 1988 ዓ.ም. የቀረበው ይህ የዳግም-ትመና ሪፖርት እንደሚያስረዳው፡፡<br><br>ሀ) የመጀመሪያውን ጥናት ያዘጋጁት አቶ ውድነህ አስቤና አቶ ሰለሞን ወሴን በማስቀረት አቶ ባደግ ከበደና አቶ ተሾመ ዱብሬ የተባሉ ሁለት ባለሙያዎች ጥናቱን ከፋብሪካው ማኔጅሜንት ጋር እንደገና መርምረውታል፡፡<br><br>ለ) የንብረት ቆጠራውን ከታህሳስ 30/1987 ወደ የካቲት 30/1987 በማዞር፣ በመለዋወጫ፣ በጥሬ ዕቃና በመሳሰሉት ላይ የተወሰነ ለውጥ መገኘቱን፤<br><br>ሐ) በቋሚ ንብረቶች በኩል ደግሞ ቀደም ሲል ያልተካተቱ አምስት ጐተራዎችና አንድ ሚዛን ተጨማሪ እንደተገኙ፣ እንደዚሁም አንድ ተጨማሪ ተሽከርካሪ እንደተገኘ፤<br><br>መ) በዚህ የተነሳ ጠቅላላ ውጤቱ ወደ ብር 8,777,051.07 (ስምንት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ሰባት ሺህ ሃምሳ አንድ ከሰባት ሣንቲም) ከፍ ያለ ስለመሆኑና ተጨማሪ የተባሉት ንብረቶችም በዝርዝር እንደተያያዙ ተገልጿል፡፡<br><br>ኤጀንሲው ርክክቡን ያስጀመረው፣ የሽያጭ ውሉ በሚያዘው መሠረት በትርፍነት ለተገኙት ንብረቶች ገዢ ዋጋቸውን እንደሚከፍል ካረጋገጠና ካስተመነ በኋላ ነበር የሥራ አመራር ቦርድ በብር 2,041,104.86 እንዲሸጡ የወሰነባቸው ጎተራዎች በዚህ ወቅት የተገመቱት ከ 1 ሚልዮን በታች እንደነበረም መረዳት ይቻላል። ኤጀንሲው በዚህ መሠረት ተገቢውን ማስተካከያ አድርጐ፣ ፋብሪካው በመጨረሻ ላይ የተሸጠው በብር 8 ሚሊዮን ሳይሆን ከ10 ሚሊዮን በላይ በሆነ ዋጋ መሆኑ እየታወቀ ሀቁን በመሸፋፈን የቀረበው ክስ የሐሰት ለመሆኑ ግልፅ ነው፡፡<br>62.2 ዐቃቤ ህግ ላቀረበው ክስ ማስረጃ እንዲሆነው፤ የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካን እንደገና በማስተመን ሪፖርቱን በማስረጃነት ለዚሁ ፍ/ቤት አቅርቦት ነበር፤ ሪፖርቱን ያዘጋጁት ግለሰቦችም ቀርበው መስክረዋል። በዚህ የዋጋ ግምት ውጤት መሠረት ኤጀንሲው የተጠቀመበትን የመተኪያ ዋጋ ዘዴ በመጠቀም በትርፍነት ለተገኙት አምስት ጎተራዎች ያገኘው ውጤት ብር 1,656,006.20 ስለመሆኑ በሪፖርቱ በተለይ ደግሞ አባሪ 2/2 ሆኖ በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ ተገልጿል። ለእነዚህ ጎተራዎች ቦርዱ የተሰማማበት ዋጋ ግን ብር 2,041,104.86 በመሆኑ፤ ኮሚሽኑ ካቀረበው ዋጋም እጅጉን ከፍ ያለ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። |
| 63 | 63.1 የኢትዮጵያ ፕ ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣ | 63.1 የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ዋጋ ትመና ሲሰራ ያልተካተቱና በርክክብ ወቅት የተካተቱት ጐተራዎች፣ የሚሸጡበት ዋጋ የተወሰነው በ1ኛ ተከሳሽ እንደሆነ በማስመሰል ዐቃቤ ሕግ በክሱ ላይ አቅርቧል፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ ቃለ ጉባዔ መረዳት እንደሚቻለው፣ ገዥና ሻጭ በዋጋ ተመኑ ላይ ስላልተግባቡና በተለይ ገዥ፣ ኤጀንሲው የሰጠው ተመን ከፍተኛ ነው |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | ቃለ ጉባዔ ቁጥር 52 ( 8 ገፅ)፣ ሐምሌ 2 ቀን 1989 ዓ.ም.<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>D – 26<br><br>63.2 የኢትዮጵያ ኘ ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣<br>ቃለ ጉባዔ ቁጥር 48 (11 ገፅ)፣ መጋቢት 10 ቀን 1989 ዓ.ም.<br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br>D – 12 | በሚል ለሥራ አመራር ቦርዱ አቤቱታ እንዳቀረበ ነው:: አቤቱታውን መርምሮ የመወሰን ሥልጣኑና ሃላፊነቱ በአዋጅ የተጣለበት ቦርድ፣ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ፣ ገዢ የጠቀሰው ብር 547,402.73 (አምስት መቶ አርባ ሰባት ሺህ አራት መቶ ሁለት ከሰባ ሦስት) በጣም እንዳነሰ፣ ኤጀንሲው የጠየቀው ብር 3,025,802.00 (ሦስት ሚሊዮን ሃያ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሁለት) ደግሞ ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ፣ ቀደም ሲል ገዢም ጠቅሰውት የነበረውን ብር 2,041,104.86 (ሁለት ሚሊዮን አርባ አንድ ሺህ አንድ መቶ አራት ከሰማንያ ስድስት ሣንቲም) እንዲከፍሉ ወስኗል:: ስለሆነም::<br><br>ሀ) ውሣኔው የሰጠው 1ኛ ተከሳሽ አስመስሎ ያቀረበው ክስ ሐሰተኛ ነው፣ የቦርዱ ውሣኔ ደግሞ ሕጋዊም ምክንያታዊም ስለሆነ ሊነቀፍበት አይገባም፤<br><br>ለ) □ ተራዎቹ ባለመካተታቸው ያነሰ መስሎ የታየውና ትችት አስነሳ የተባለው የፋብሪካው ዋጋም ብር 8 ሚሊዮን መሆኑ ቀርቶ ከብር 10 ሚሊዮን በላይ ከፍ አድርጉታል::<br><br>ይህ የሥራ አመራር ቦርድ የተስማማበት አሃዝ ገዢ ከጠቀሰው ብር 547.402.73 እጅግ በጣም ከፍያለ፤ ማስረጃ ተ.ቁ. 62.1 እና 62.2 ላይ ከተጠቀሱት የኤጀንሲው እና የዋናው ኦዲተር ተመኖችም በጣም ከፍ ያለ ሆኖ ኤጀንሲው ገዢውን እንዲከፍል ጠይቆት ከነበረው አሃዝ ግን ዝቅ ያለና ሚዛኑን የጠበቀ ለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል።<br>ይህ ውሳኔ የቦርዱ አባላት የሆኑት፤<br>• አቶ አሰፋ አብርሃ<br>• ዶ/ር ከበደ ታደሰ<br>• አቶ ሱፊያን አህመድ<br>• አቶ ጥላሁን አባይና<br>• አቶ በሻህ አዝምቴ በሙሉ ድምፅ የወሰኑት ለመሆኑ ቃለ ጉባኤው ያስረዳል።<br><br>63.2 የሥራ አመራር ቦርዱ የማንኛውም ተጫራች ይግባኝ አይቶ የመወሰን የህግ ግዴታ የተጣለበት እንደመሆኑ፤ ይግባኝን መመርመር እና ውሳኔ መስጠት አንድ ዋና ተግባሩ ነው። የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ከገዙት ባለሀብት ጋር የተነሣው አይነት ክርክር የፔፕሲ ኮላ ፋብሪካዎችን ከገዛው ባለሃብት ጋርም ተነስቶ ነበረ። ይህ ክርክር ለሥራ አመራር ቦርዱ ቀርቦ በዚሁ በ48 ቃለ ጉባኤ ላይ ውሳኔ አግኝቷል። በቃለ ጉባኤው ገፅ 8 እና 9 ላይ እንደሚነበበው ኤጀንሲው ገዢውን ክፈል ብሎ የጠየቀው የማስተካከያ ሂሳብ ብር 8.768.069.84 ነበረ። ይሁን እንጂ ቦርዱ የተቀበለው እና ገዢም እንዲከፍል የተስማማው ብር 6.147.356.41 ብቻ ነው። ይህ አሰራር በደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ላይ ብቻ የተከሰተ አዲስ ነገር አለመሆኑን ከዚህ መረዳት ይቻላል። |
| 64 | የኢትዮጵያ ኘ ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ በገተራዎቹ ላይ የቀረበለትን | 64. የኤጀንሲው ተጠሪነት ለጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት ስለመሆኑ በአዋጁ በግልፅ ተደንግጓል:: የኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ አባላት፣ የኤጀንሲው ሥራ አስኪያጅና የሥራ ሃላፊዎች፣ እንዲሁም ፀሃፊዎችና ባለሙያዎች በሙሉ የተመደቡት በዚሁ ጽ/ቤት ከመሆኑ በተጨማሪ ኤጀንሲው ስለኘሮግራሙ አፈፃፀምና ዕቅድም በቀዳሚነት ሪፖርቱን የሚያቀርበው ለዚሁ ጽ/ቤት ነው:: |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | ይግባኝ መርምሮ የወሰነበት ቃለ ጉባዔ ቁጥር 52 በወቅቱ ለጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት የተላከከ ስለመሆኑ የሚያረጋግ ደብዳቤ፤<br>/ 1 ገፅ/<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>D - 27 | ከዚሁ በተጨማሪ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ሆነው ከ1986 እስከ 1987 ድረስ ያገለገሉት አቶ ተከስተብርሃን ገ/ሚካኤልም ሆነ ከ1987 እስከ 1993 ያገለገሉት አቶ አሰፋ አብርሃ በጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት የኢኮኖሚ ዘርፍ፣ እንደቅደም ተከተላቸው ሃላፊና አባል ሆነው የሠሩ ነበሩ:: በተለይ ከ1988 ዓ.ም. ጀምሮ የኤጀንሲው የቦርድ አባላት ሆነው የሰሩት እነ አቶ ተፈራ ዋልዋ፣ ዶ/ር ከበደ ታደሰ፣ አቶ መስፍን ለማ፤ አቶ ሙሉጌታ ዓለምሰገድና አቶ ቢተው በላይ በጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት በተለያዩ ዘርፎች በሃላፊነት የሚሠሩ ነበሩ:: አቶ ማሕተመ ሰለሞንና አቶ ሱፍያን አህመድ ደግሞ የካቢኔ አባል ሚኒስትሮች ነበሩ:: እነዚህ የኤጀንሲው ሃላፊዎችና የቦርድ አባላት ለጽ/ቤቱ ከሚያቀርቡት የቃልና የፅሑፍ ሪፖርት በተጨማሪ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ቃለ ጉባዔዎች በበቂ ኮፒ ተባዝተውና ተፈርሞባቸው ከሽኚ ደብዳቤ ጋር ለጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት በየወቅቱ ይላካሉ:: ከዚህ ሁሉ በመነሳት:-<br><br>ሀ) የጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት እንደአካል፣ እንደዚሁም ጠ/ሚኒስትሩና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሃላፊዎች በሙሉ በሂደቱ በቀጥታ የተሳተፉና ስለእያንዳንዱ ሽያጭ በዝርዝር እያወቁ መመሪያና ውሣኔ ሲሰጡ የነበሩ ለመሆኑ ግልፅ ነው::<br>ለ) ከ1987 ዓ.ም. እስከ 1988 ዓ.ም. ለተፈፀሙት ሽያጮት በሙሉ፣ የኤጀንሲው ሥራ አመራር ቦርድ ያቀረባቸውን ሃሣቦች ከቃለ ጉባዔውና ከመግለጫዎቹ ከገመገመ በኋላ ጽ/ቤቱ የመጨረሻ ውሣኔዎቹን በፅሑፍ ለኤጀንሲው ያሳወቀ ሲሆን፣ የድሮው ቦርድ ፈርሶ ከፍ ብለው የተጠቀሱት ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች በቦርድ አባልነት ከተመደቡበት ከ1988 ዓ.ም. በኋላ ደግሞ ውሣኔውን በም/ጠ/ሚ/ር በኩል በቃል እያረጋገጠ ነው ሽያጭ የተፈፀመው::<br>[illegible]) በዚህ አንፃር ደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካን ጨምሮ መንግሥት ሳያውቅ ወይም ሳይፈቅድ የተሸጠ ድርጅት እና የተፈፀመ የቦርድ ውሣኔን ያለ በማስመሰል የቀረበው የዐቃቤ ሕግ ክስ መሠረት የሌለው ነገር ለመሆኑ ግልፅ ነው:: |

5. <u>ጉለሌ ሣሙና ፋብሪካን በሚመለከት፤</u>

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| 65 | <u>በጨረታ ቁጥር 001/89 የጉለሌሣሙና ፋብሪካ የጨረታ ሰነድ (በከፊል የቀረበ)</u><br>በዚህ ስር የተጠቀሱት ሰነዶች፤ የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br>65.1 የጨረታ ማስታወቂያ<br>/ 1 ገፅ/<br>G -01 | 65. የጉለሌ ሣሙና ፋብሪካ ለጨረታ ሲቀርብ፣ ተጫራቾች እስከ 100% ድርሻ ድረስ ለፈለጉት የድርሻ መጠን እንዲወዳደሩ በሚጋብዝ መልኩ ነበረ:: ስለሆነም ምናልባት ገዢዎች ያሸነፉት ከ100% ላነሠ ድርሻ ሆኖ የአክሲዮን ኩባንያ ማቋቋም ቢያስፈልግ ተብሎ፣ የአክስዮን ኩባንያ ማቋቋሚያ ሰነዶችም በጨረታ ሰነዱ ዝርዝር ተካትተው ቀርበው ነበር:: ከዚህ በተጨማሪ ከክሱ አንፃር የቀረቡት ሁለት ሰነዶች የሚከተለውን ያስረዳሉ::<br><br>65.1 በጨረታ ማስታወቂያው ላይ አብረው ለሽያጭ የቀረቡት 8 ድርጅቶች ሲሆኑ፣ አብዛኞቹ በተደጋጋሚ ለሽያጭ ቀርበው ገዢ ያልቀረበላቸው ነበሩ፣ ጉለሌ ሣሙና ፋብሪካ ራሱ በጨረታ ቁጥር 001/1989 ሲወጣ ለሦስተኛ ጊዜው ነበር:: በጨረታ ማስታወቂየው በግልፅ እንደተቀመጠው ጨረታው ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ሀገር ባለሀብቶች በሙሉ ክፍት የሆነ ነበረ፣ መንግሥት በዚህ ጨረታ መሸጥ የሚፈልገው የፋበሪካው ሙሉ የባለቤትነት ድርሻ ወይም እስከ 100% ሆኖ፣ ተጫራቾች ግን ለሚችሉት ያህል መጫረት እንደሚችሉ በግልፅ ታውጇል:: የየፋብሪካው መነሻ ዋጋ በጨረታ ሰነዱ የተገለፀ መሆኑም ተገልጿል:: |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | 65.2 የተጫራቾች መመሪያ<br>/ 11 ገፅ/<br>G -02 | ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለው:-<br>ሀ) እያንዳንዱ ተጫራች እስከ 100% ለፈለገው መጠን መጫረት እንደሚችል በግልፅ ተቀመጠ እንጂ፣ ከፍተኛ የአክስዮን መጠን የገዛ ያሸንፋል አልተባለም:: ስለሆነም ለ51% መወዳደርና ለ100% መወዳደር፣ የተጫራቾች ምርጫ እንጂ <u>የአሸናፊነት መመዘኛ</u> አይደለም::<br>ለ) በጨረታ ቁጥር 004/87 ለደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ያልተገለፀ፣ እዚህ ላይ ግን መነሻ ዋጋ የተቀመጠ ለመሆኑ በግልፅ ታውጇል፣ ስለዚህ ኤጀንሲው መነሻ ዋጋ ያስቀመጠ ዕለት በጨረታ ማስታወቂያ ላይ ይገለፃል::<br><br>65.2 የተጫራቾች መመሪያ ሆኖ በቀረበው ሰነድ ላይ ስለጨረታው አቀራረብ፣ ግምገማ፣ ▯▯ የአሸናፊነት ምርጫ ሂደት ዝርዝር አንቀጾች ቀርበዋል::<br><br>▯) በተለይ በአንቀፅ 4 ላይ ማንኛውም ተጫራች በዚህ ጨረታ ሲወዳደር ለሚያወጣው ወጪ ሁሉ፣ ራሱ ሃላፊ እንደሚሆን በግልፅ ተቀምጧል:: ተወዳድሮ የተሸነፈ ሁሉ ጉዳት ደረሰብኝ ብሎ ኤጀንሲውን ወይም ሌላን አካል መጠየቅ እንደማይችል ግልፅ ሆኖ እያለ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ <u>ተወዳድረው በተሸነፉት ሰዎች ላይ</u> ጉዳት እንዳደረሰና ለጉዳቱም ተከሳሾችን ተጠያቂ ለማድረግ መሞከሩ ተቀባይነት አይገባውም፤<br>ለ) መንግሥት መሸጥ የሚፈልገው እስከ 100% ድረስ ሆኖ ተጫራቾች ግን ለፈለጉት የድርሻ መጠን መወዳደር እንደሚችሉ በአንቀፅ 8 ሥር በግልፅ ታውጇል::<br>▯) በጨረታው አሸናፊ የሚመረጠው «<u>የዋጋ ብልጫን መሠረት በማድረግ</u>» ስለመሆኑም በአንቀፅ 14.2 ላይ በግልፅ ተቀምጦ እያለ፣ ዐቃቤ ሕግ በአክስዮን ብዛት አሸናፊ መመረጥ ነበረበት ብሎ ያቀረበው ክስ መሠረተ ቢስ ነው:: የጨረታ ኮሚቴው በዋጋ ብልጫ አሸናፊ የሆነውን በመተው 100% እንገዛ ላሉት እንዲሸጥ ያቀረበው የውሳኔ ሃሣብ ከመመሪያው ጋር የሚቃረን ለመሆኑም ግልፅ ነው ። የስራ አመራር ቦርዱ ይህን የተሣሣተ ሃሳብ አልቀበልም ማለቱም ትክክል ነበረ። |
| 66 | የኢትዮጵያ ፕ ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 44 (10 ገፅ)፣ ሕዳር 25 ቀን 1989 ዓ.ም.<br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br>G -03<br><br>66.1 ህዳር 27 ቀን 1989 ዓ.ም ከኤጀንሲው ለአቶ ፍፁምዘአብ አስገዶም | 66. ይህ 44ኛው የቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባዔ፣ በተለይ የጉለሌ ሣሙና ፋብሪካን በሚመለከት፤ የሚከተሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች ያስረዳል።<br><br>66.1 በዚህ ቃለ ጉባዔ ገፅ 12 ጀምሮ በዝርዝር የቀረበው ሌላ ጉዳይ የጉለሌ ሣሙና ፋብሪካን ሽያጭ የሚመለከተው ነው:: በጨረታ ቁጥር 001/89 ላይ ለሽያጭ ከቀረቡት 8 ድርጅቶች ውስጥ የጉለሌ ሣሙና ፋብሪካ እንደሚገኝ፣ ከስምንቱ ፋብሪካዎች ውስጥ ገዢ የቀረበላቸው ሦስቱ ብቻ ሲሆኑ፣ ለአምስቱ ፋብሪካዎች አንድም ተጫራች እንዳልቀረበላቸውም ተዘግቧል:: ጉለሌ ሣሙና ፋብሪካ ከዚህ ጨረታ በፊት ሁለት ጊዜ ቀርቦ ገዢ ባይቀርብለትም በዚሁ በሦስተኛው ጨረታ ግን ሁለት ገዢዎች እንደቀረቡለትም ተዘግቧል:: እነዚህ ሁለት ተጫራቾች ያቀረቡት ዋጋ መነሻ ሆኖ ከተቀመጠው የኤጀንሲው ተመን ከፍ ያለ ሲሆን፣ አቶ ዱግማ ሁንዴና አቶ ጌቱ ገለቱ የተባሉት ተጫራቾች ባንድነት ያቀረቡት ዋጋ ለ100% |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | የተፃፈ ደብዳቤ /1 ገፅ/<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>G -04<br><br>66.2 ታህሳስ 3 ቀን 1989 ዓ.ም ከአቶ ፍፁምዘአብ አስገዶም ለኤጀንሲው የተፃፈ መልስ / 1 ገፅ /<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>G -05 | የባለቤትነት ድርሻ ብር 21,566,042.00፣ ወደ 1% ተካፍሎ ሲሰላ ብር 215,660.42 እንደሆነ፣ አቶ ፍፁምዘአብ አስገዶም ያቀረቡት ዋጋ ደግሞ ለ51% የባለቤትነት ድርሻ ብር 11,408,700.00 ፣ ወደ 1% ተካፍሎ ሲሰላ ደግሞ ብር 223,700 በመሆኑ አሸናፊ ስለመሆኑ ተዘግቧል:: አሸናፊ የሚመረጠው ዋጋን ብቻ መሠረት በማድረግ እንደሆነ በሚደነግገው የጨረታ መመሪያ መሠረት የዚህ ጨረታ <u>አሸናፊ አቶ ፍፁምዘአብ አስገዶም ቢሆኑም</u> እገዛለሁ ብለው ያቀረቡት የፋብሪካውን 51% ድርሻ ብቻ በመሆኑ፣ በዚሁ ዋጋ ቀሪውን 49% በመጠቅለል ለመግዛት <u>ይፈልጉ እንደሆነ ተጠይቀው ፈቃደኛ ከሆኑ</u> የፋብሪካው 100% ድርሻ በብር 22,370,000.00 እንዲሸጥላቸው፣ ፈቃደኛ ካልሆኑ ግን የፋብሪካውን 100% በብር 21,566,042.00 እንገዛ ብለው ላቀረቡት ለእነ አቶ ጌቱ ገለቱ እንዲሸጥ ቦርዱ የወሰነ ስለመሆኑም በግልፅ ተቀምጧል:: በዚህ የቦርድ ውሳኔ ላይ የተሳተፉት፤<br>• አቶ አሰፋ አብርሃ<br>• ዶ/ር ከበደ ታደሰ<br>• አቶ ሱፊያን አህመድ<br>• አቶ ማህተመ ሰለሞን<br>• አቶ ጥላሁን አባይና<br>• አቶ በሻህ አዝምቴ ስለመሆናቸው ቃለ ጉቤኤው ያስረዳል።<br>66.2 ይህን ሀቅና የቦርድ የጋራ ውሣኔ መሠረት አድርገን የዐቃቤ ሕግን ክስ ስንመረምር፤<br><br>ሀ) የዚህ ድርጅት ሽያጭ የተፈፀመው ከቦርዱ እውቅና ውጭ በ1ኛ ተከሳሽ ትእዛዝና ውሣኔ አንደሆነ በማስመሰል የቀረበው ክስ ሐሰት ነው፤<br>ለ) እነ አቶ ጌቱ ገለቱ አሸናፊ ተብለው እንደተወሰነላቸው፣ ይኸው ውሣኔም እንደተገለፀላቸው ሆኖ የቀረበውም ሐሰት ነው፤<br>ሐ) አቶ ፍፁምዘአብ አስገዶም ተሸናፊ ተብለው እንደተተዉና ከዚያ በኋላ በልዩ ሁኔታ አሸናፊ እንደሆኑ ተደርጐ የቀረበውም ሐሰት ነው፤<br>መ) በዚህ ውሣኔ በእነ አቶ ጌቱ ገለቱ ላይ አድልዎ እንደተፈፀመ፣ ልዩ ጉዳትም እንደደረሰባቸው ተደርጐ የቀረበውም መሠረተ ቢስ ነው::<br>ሠ) በተመሣሣይ መልኩ ለፋብሪካው የተሻለ ዋጋ የተገኘ መሆኑ ግልፅ እያለ፣ በመንግሥት ጥቅም ላይ ጉዳት እንዳደረሰ ሆኖ የቀረበው ክስም መሠረተ ቢስ ነው፤<br><br>66.3 ቦርዱ ውሣኔውን የሰጠው የጨረታ መመሪያውን መሠረት በማድረግና በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን ሣያልፍ በመሆኑ፣ ውሣኔው የሚነቀፍበት ምክንያት የለም:: ስለዚህ በውሣኔው የተጣሰ ሕግ፣ መመሪያም ሆነ አሠራር የለም:: አላግባብ የተጠቀመ ወገን ያለመኖሩን ያህል የተጐዳ ወገንም የለም::<br><br>66.4 ከዚህ በተጨማሪ ቦርዱ በጉዳዩ ላይ ለመወሰን ሲሰየም፤ አቶ ፍፁምዘአብ ለ51 ፐርሰንት ባቀረቡት ዋጋ 100 ፐርሰንት ልግዛ የሚል ማመልከቻ በኤጀንሲው ሥራ አስኪያጅ በኩል ለቦርድ እንደቀረበ ሆኖ የቀረበው እና በዚሁ መሠረት ብዙ ክርክርና የድምፅ ልዩነት እንደተፈጠረ ሆኖ የቀረበው የአቶ ማህተመ ሰለሞን ምሥክርነት የተሣሣተ ስለመሆኑ፤ በተጫራቹና በኤጀንሲው መካከል ከተደረገው መፃፃፍ እንደሚከተለው ማረጋገጥ ይቻላል ።<br>ሀ) ሥራ አመራር ቦርዱ በፋብሪካው ሽያጭ ላይ ተወያይቶ፤ ለ51% ባቀረቡት ዋጋ |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | | የፋብሪካውን 100% ለመግዛት ፈቃደኛ ከሆኑ ተጠይቀው፤ ከተስማሙ ፋብሪካው ለአቶ ፍፁምዘአብ አስገዶም እንዲሸጥ የወሰነው፤ በ44ኛ ስብሰባው ሕዳር 25 ቀን 1989 ዓ.ም ነበር። <br> ለ) በዚሁ መሠረት፤ ለ51% ባቀረቡት ዋጋ የፋብሪካው 100% ለመግዛት ይፈልጉ እንደሆነ ኤጀንሲው ለአቶ ፍፁምዘአብ አስገዶም ጥያቄውን የላከላቸው ህዳር 27 ቀን 1989 ዓ.ም መሆኑ ደብዳቤው ያረጋግጣል። <br> ሐ) ከዚያ በኋላ አቶ ፍፁምዘአብ አስገዶም ለቀረበላቸው ጥያቄ ስምምነታቸውን ያረጋገጡት ደግሞ ታህሳስ 3 ቀን 1989 በሰጡት የፅሁፍ መልስ ነው። |
| 67 | የኢትዮጵያ ኘ ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣ <br> ቃለ ጉባዔ ቁጥር 45 ( 4 ገፅ)፣ ታህሳስ 16 ቀን 1989 ዓ.ም. <br><br> የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል። <br><br> G -06 | 67. የኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ፣ የጉለሌ ሣሙና ፋብሪካ ሽያጭን በተመለከተ አቶ ፍፁምዘአብ የፋብሪካውን 100% የባለቤትነት ድርሻ ለ51% በሰጡት ነጠላ ዋጋ መሠረት ለመግዛት ፈቃደኛ ስለመሆናቸው ተጠይቀው ከተስማሙ እንዲሸጥላቸው የወሰነ ስለመሆኑ በማስረጃ ተራ ቁጥር 66 ላይ አይተናል:: በዚህ ውሣኔ መሠረት አቶ ፍፁምዘአብ አስገዶም በኤጀንሲው በኩል ተጠይቀው የተስማሙ ለመሆናቸው ደግሞ በዚሁ በ45ኛው የቦርዱ ቃለ ጉባዔ ገፅ 4 ላይ ተዘግቧል::: <br> ሀ) የጉለሌ ሣሙና ፋብሪካ ለአቶ ፍፁምዘአብ አስገዶም የተሸጠው በ1ኛ ተከሳሽ ድጋፍ፣ ትእዛዝ ወይም ውሣኔ ሳይሆን የሥራ አመራር ቦርድ በሰጠው ውሣኔ መሠረት ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል:: <br> ለ) አቶ ማህተመ ሰለሞን የተባሉት የዐቃቤ ህግ ምሥክር፤አቶ ፍፁምዘአብ ለ51 በሰጠው ዋጋ 100 ልግዛ ብሎ ጠይቋል የሚለው ጉዳይ ቦርድ በፋብሪካው ሽያጭ ላይ ለመወሰን ለተሰበሰበው ለ44ኛው ስብሰባው በኤጀንሲው ሥ/አስኪያጅ በኩል ቀርቦ እንደነበረ በማስመሰል የሰጡት ቃል የተሣሣተ ለመሆኑና አቶ ፍፁምዘአብ ተጠይቀው እሺ ያሉት ከቦርድ ውሳኔ በኋላ መሆኑን ያስረዳል። |
| 68 | የኢትዮጵያ ኘ ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ በጉለሌ ሣሙና ፋብሪካ ሽያጭ ላይ ተወያይቶ ውሣኔ የሰጠባቸው ቃለ ጉባዔዎች ቁጥር 44፣45 እና 46 በወቅቱ ለጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት የተላኩ ስለመሆናቸው የሚያረጋግጥ ደብዳቤ፤ / 1 ገፅ / <br><br> የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል። | 68. የኤጀንሲው ተጠሪነት ለጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት ስለመሆኑ በአዋጁ በግልፅ ተደንግጓል:: የኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ አባላት፣ የኤጀንሲው ሥራ አስኪያጅና የሥራ ሃላፊዎች፣ እንደዚሁም ፀሃፊዎችና ባለሙያዎች በሙሉ የተመደቡት በዚሁ ጽ/ቤት ከመሆኑ በተጨማሪ ኤጀንሲው ስለኘሮግራሙ አፈፃፀምና ዕቅድም በቀዳሚነት ሪፖርቱን የሚያቀርበው ለዚሁ ጽ/ቤት ነው:: ከዚሁ በተጨማሪ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ሆነው ከ1986 እስከ 1987 ድረስ ያገለገሉት አቶ ተከስተብርሃን ገ/ሚካኤልም ሆነ ከ1987 እስከ 1993 ያገለገሉት አቶ አሰፋ አብርሃ በጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት የኢኮኖሚ ዘርፍ፣ እንደቅደም ተከተላቸው ሃላፊና አባል ሆነው የሠሩ ነበሩ:: በተለይ ከ1988 ዓ.ም. ጀምሮ የኤጀንሲው የቦርድ አባላት ሆነው የሰሩት እነ አቶ ተፈራ ዋልዋ፣ ዶ/ር ከበደ ታደሰ፣ አቶ መስፍን ለማ፤ አቶ ሙሉጌታ ዓለምሰገድና አቶ ቢተው በላይ በጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት በተለያዩ ዘርፎች በሃላፊነት የሚሠሩ ነበሩ:: አቶ ማሕተመ ሰለሞንና አቶ ሱፍያን አህመድ ደግሞ የካቢኔ አባል ሚኒስትሮች ነበሩ:: እነዚህ የኤጀንሲው ሃላፊዎችና የቦርድ አባላት ለጽ/ቤቱ ከሚያቀርቡት የቃልና የፅሑፍ ሪፖርት በተጨማሪ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ቃለ ጉባዔዎች በበቂ ኮፒ ተባዝተውና ተፈርሞባቸው ከሽኚ ደብዳቤ ጋር ለጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት በየወቅቱ ይላካሉ:: ከዚህ ሁሉ በመነሳት:- <br><br> ሀ) የጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት እንደአካል፣ እንደዚሁም ጠ/ሚኒስትሩና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሃላፊዎች በሙሉ በሂደቱ በቀጥታ የተሳተፉና ስለእያንዳንዱ ሽያጭ በዝርዝር እያወቁ |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | G -07 | መመሪያና ውሣኔ ሲሰጡ የነበሩ ለመሆኑ ግልፅ ነው::<br>ለ) ከ1987 ዓ.ም. እስከ 1988 ዓ.ም. ለተፈፀሙት ሽያጮት በሙሉ፣ የኤጀንሲው ሥራ አመራር ቦርድ ያቀረባቸውን ሃሣቦች ከቃለ ጉባዔውና ከመግለጫዎቹ ከገመገመ በኋላ ጽ/ቤቱ የመጨረሻ ውሣኔዎቹን በፅሑፍ ለኤጀንሲው ያሳወቀ ሲሆን፣ የድሮው ቦርድ ፈርሶ ከፍ ብለው የተጠቀሱት ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች በቦርድ አባልነት ከተመደቡበት ከ1988 ዓ.ም. በኋላ ደግሞ ውሣኔውን በም/ጠ/ሚ/ር በኩል በቃል እያረጋገጠ ነው ሽያጭ የተፈፀመው::<br>በዚህ አንፃር በተለይ የጉለሌ ሣሙና ፋብሪካ ሺያጭ መንግሥት ሳያውቅ ወይም ሳይፈቅድ የተፈፀመ በማስመሰል የቀረበው የዐቃቤ ሕገ ክስ መሠረት የሌለው ነገር ለመሆኑ ግልፅ ነው:: |
| 69 | የኢትዮጵያ ን ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣<br>ቃለ ጉባዔ ቁጥር 21 (5 ገፅና 1 ገፅ አባሪ) ፣<br>ሰኔ 26 ቀን 1987 ዓ.ም.<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>D - 07 | 69. ከጉለሌ ሣሙና ፋብሪካ በፊት የወጣው የጨረታ ቁጥር 004/87 መመሪያ፣ ማንኛውም ተጫራች ከ1% እስከ 75% ለፈለገው የባለቤትነት ድርሻ እንዲወዳደር ከመፍቀዱ በተጨማሪ አሸናፊ የሚመረጠውም በዋጋ መሆኑን ይደነግጋል:: በዚህ መሠረት ለአድዋ ዱቄት ፋብሪካ እና ለትግራይ ዱቄት ፋብሪካ የቀረቡት ተጫራቾች የተወዳደሩት ለተለያዩ የባለቤትነት ድርሻ መጠኖች በተሰጡ የተለያዩ ዋጋዎች ስለነበረ፣ ኤጀንሲው አሸናፊውን ለመለየት ዋጋዎቹን <u>ወደ 1% በመቀየር እርስ በእርስ በማነፃፀር</u> እንደሆነ በዚሁ ቃለ ጉባዔ ይነበባል:: በዚህ መሠረት አሸናፊ የተመረጠው ነጠላ ዋጋዎቹን በማነፃፀር በመሆኑ፤<br>[illegible]) በተመሣሣይ መልኩ በጉለሌ ሣሙና ፋብሪካ ጨረታ ላይ አንዱ ተጫራች ለ100% ድርሻ፣ ሌላኛው ደግሞ ለ51% ድርሻ መወዳደራቸው የሚፈቀድና የተለመደ ለመሆኑ፤<br>[illegible]) አሸናፊውን ለመለየት ዋጋውን ወደ 1% በመቀየር ማነፃፀርና መምረጥም የተለመደና የሚታወቅ አሠራር እንደመሆኑ፤<br>በጉለሌ ሣሙና ፋብሪካ ጨረታ ላይ የተለየና አድሎአዊ ነገር እንደተፈፀመ ተደርጐ መቅረቡ መሠረተ ቢስ መሆኑን ያስረዳል፤ |
| 70 | የኢትዮጵያ ን ራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፣ የሥራ አመራር ቦርድ ስብሰባ፣<br>ቃለ ጉባዔ ቁጥር 24 (6 ገፅ )፣<br>ነሐሴ 30 ቀን 1987 ዓ.ም.<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>G – 08 | 70. ይህ 24ኛው ቃለጉባዔ የሚከተለውን ያስረዳል::<br><br>የኤጀንሲው የጨረታ መመሪያዎች፣ ለጉለሌ ሣሙና ፋብሪካ የወጣው መመሪያን ጨምሮ፣ ከ100% የየድርጅቱ የባለቤትነት ድርሻ ውስጥ ተጫራቾች ለሚፈልጉት መጠን ብቻ እንዲወዳደሩ ይፈቅዳሉ:: ተጫራቾች በዚህ መመሪያ መሠረት ለተለያየ ድርሻ የተጫረቱ ጊዜ አሸናፊ ለመለየት ንፅፅር የሚደረገው የሁሉም ተጫራቾች ዋጋ ወደ 1% ድርሻ በመቀየር ነው:: በዚህ መንገድ ተነፃፅሮ የአቶ ፍፁምዘአብ አስገዶም ዋጋ በጉለሌ ሣሙና ፋብሪካ ላይ አሸናፊ እንደተባለው ሁሉ፣ ለአንበሳ ዱቄት ፋብሪካ ግዢ አራት ተጫራቾች ለተለያዩ ድርሻዎች ሲወዳደሩ ዋጋቸውን ወደ 1% በመቀየር ንፅፅር ተደርጐ አሸናፊው እንደተመረጠ ቃለ ጉባዔ ቁጥር 24 ያስረዳል:: በተመሣሣይ መልኩ ለአድዋ ዱቄት ፋብሪካ የተደረገው ንፅፅርም በዚሁ መንገድ ለመሆኑ ማስረጃ ተራ ቁጥር 69 ሆኖ የቀረበው ቃለ ጉባዔ ቁጥር 21 ያስረዳል:: |

## 8. <u>ሁሉንም ድርጅቶች በሚመለከት፤</u>

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| 71 | የኦዲተሮች ቡድን ጣይቱ ሆቴል፤ ሐረር ማተሚያ ቤት፤ ደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካና ጉለሌ ሳሙና ፋብሪካ ፕራይቬታይዝ የተደረጉበትን ሁኔታ በተመለከተ ምርመራ አካሄዶ የሚያቀርበው ሪፖርት / በዝግጅት ላይ የሚገኝ / <br> A - 01 | 71. ሪፖርቱ ተጠናቅቆ ሲቀርብ፤ ዝርዝር መግለጫ እናቀርብበታለን። በአጠቃላይ ግን በፍ/ቤቱ ብይን ላይ የተጠቀሱትን ጉዳዮች በተመለከተ በዝርዝር ያስረዳል። |
| 72 | አቶ ማህተመ ሰለሞን የተባሉት የዐቃቤ ህግ ምሥክር ህዳር 27 ቀን 1995 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ ከሰጡት ቃል ውስጥ በከፊል የቀረበ / 5 ገፅ/ <br> የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል። <br> /1፣3፣52፣53፣54. / <br> A - 02 | 72. ምሥክሩ፤በተለይ በጉለሌ ሣሙና ፋብሪካ ላይ የሥራ አመራር ቦርዱ ያደረገውን ውይይት በተመለከተ በርካታ የተሣሣቱና ከቃለ ጉባኤውም ሆነ ከሌሎች የቦርድ አባላት ቃል ጋር የማይጣጣም ቃል ሰጥተዋል። ቦርዱ በቀረቡለት የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ ለመወሰን ከተሰየመ በኋላ አዲስ ሃሳብ እንደቀረበና በዚሁ ዙሪያ ብዙ ክርክር እንደተደረገ አድርገው የገለፁት ስህተት ለመሆኑ፤ ቃለ ጉባኤው፤ በገዢና በኤጀንሲው መካከል የተደረጉት መፃፃፎችና ከዚያ በኋላ የተያዘው ቃለ ጉባኤ ግልፅ አድርገውታል። በዚሁ መሰረትም ቦርዱ በ44ኛው ስብሰባ ላይ ሲወያይ 51% የነበረውን ወደ 100% ከፍ አድርጌ ልግዛ የሚል ሃሳብ ከአቶ ፍፁምዘአብ ያልቀረበ ስለመሆኑ፤ተጠይቀው እሺ ካሉ ይሸጥላቸው ብሎ ቦርዱ በወሰነው መሠረት ጥያቄው የቀረበላቸውና አቶ ፍፁምዘአብ የተስማሙት ከዚህ የቦርድ ስብሰባ በኋላ ስለመሆኑ፤ይኸው መልስ ለቦርዱ የቀረበው ደግሞ በ45ኛው ስብሰባ ለመሆኑ ተረጋግጧል። ከፍ ብሎ ከተጠቀሰው የተሳሳተ አባባላቸው ውጭ አቶ ማህተመ ከሰጡት ቃል በተለይ ዐቃቤ ሕግ የጥቅም ግጭት ብሎ የጠቀሰውን በተመለከተ የሚከተሉትን መረዳት ይቻላል፤ <br> ሀ) የሥራ አመራር ቦርድ የማኔጅመንት እንጂ የፍርድ አካል አለመሆኑን፤ እና የራሳቸው ዘመድ የሆነ ሰው ጉዳይ ለቦርድ ቢቀርብም ራሳቸውን እንደማያገሉ፤ ውሳኔ ከመስጠትም እንደማይከለከሉ አስረድተዋል። /ገፅ 52/ <br> ለ) በሕግ የተቀመጠ ክልከላም የሌለበት እና ነውርም እንዳልሆነ መስክረዋል። /ገፅ 53/ |
| 73 | ዶ/ር ከበደ ታደሰ የተባሉት የዐቃቤህግ ምስክር ታህሳስ 16 ቀን 1995 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ ከሰጡት ቃል ውስጥ በከፊል የቀረበ /11 ገፅ/ <br> የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል። <br> /1.2.4.5.6.12.13.14.33.34.56 / <br> A - 03 | 73. ዶ/ር ከበደ ታደሰ የጣይቱ ሆቴልን፤ጉለሌ ሳሙና ፋብሪካንና አቶ ማህተመ ሰለሞን የሰጡትን ቃል በተመለከተ የሚከተለውን አስረድተዋል። <br> ሀ) የጣይቱ ሆቴል ለጨረታ ከቀረበ በኋላ ቅርስ ነውና አይሸጥም የሚል አቤቱታ የቀረበ ለመሆኑ በዚህ ምክንያት ስለቅርስነቱ ጉዳይና ስለመሸጥ አለመሸጡ ጉዳይ መንግስት ውሳኔ እንዲሰጥበት ቦርዱ በወሰነው መሰረት ለመንግስት ጥያቄ ቀርቦ፤ ሆቴሉ ቅርስም ቢሆን እንዲሸጥ መንግስት ውሳኔ የሰጠ ለመሆኑ አረጋግጠዋል። /ገፅ 5 እስከ 6 / <br> ለ) በጉለሌ ሳሙና ፋብሪካ ሽያጭ ላይ በዋጋ አሸናፊው አቶ ፍፁምዘአብ ለመሆኑ መተማመን የተደረሰ መሆኑ፤ከዛ ባለፈ ለ51% በሰጠው ዋጋ 100% ይገዛ እንደሆ ተጠይቆ እሺ ካለ እንዲሸጥለት ቦርዱ በሙሉ ድምፅ መሰወኑን፤በዚህም የመንግስትን ጥቅም ከመጠበቁ በተጨማሪ የፋብሪካውን 100% እንዲሸጥ በማድረጉ የቦርዱ ፍላጎት የተሳካ መሆኑን፤ /ከ ገፅ 12 እስከ 14 / አስረድተዋል። <br> ሐ) ቦርዱ ይህን ውሳኔ በወሰነበት ዕለት ከተጫራቾች በኩል የቀረበ ምንም አይነት ጥያቄ እንዳልነበረ፤ይልቁንስ ለ51% ባቀረበው ዋጋ 100% ይገዛ እንደሆነ ተጫራቹ ይጠየቅ እና ፈቃደኛ ከሆነ ይሸጥለት ብሎ የወሰነው ቦርዱ ለመሆኑ አረጋግጠዋል። በዚህም አቶ ማህተመ |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | | የሰጡት ቃል የተሳሳተ መሆኑን አሳይተዋል። /ከገፅ 33 እስከ 34/ በተለይ ደግሞ አቶ ማህተመ ሰለሞን የተባሉት ሰውዬ በዚህ የቦርድ ስብሰባ ላይ የተናገሩት ወይም ያቀረቡትን ክርክርና ሃሳብ ያስታውሱ እንደሆነ እንዲያስረዱ ፍ/ቤቱ ሲጠይቃቸው ምንም የተለየ ነገር እንደማያስታውሱ መስክረዋል። /ገፅ 56/<br>መ) የስራ አመራር ቦርድ የኤጀንሲው አመራር ሰጪና መመሪያ አውጪ አካል ስለመሆኑና ውሳኔዎቹ ለኤጀንሲው መመሪያዎች ተገዢ እንዲሆኑ እንደማይጠበቅ፤ እንደማይገደድም አስረድተዋል። /ገፅ 33/ |
| 74 | አቶ ሱፍያን አህመድ የተባሉት የዐቃቤ ህግ ምስክር የካቲት 7 ቀን 1995 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ ከሰጡት ቃል ውስጥ በከፊል የቀረበ፤ / 8 ገፅ/<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>/1.23.29.30.31.34.35. 36/<br>A - 04 | 74. አቶ ሱፍያን አህመድ የተባሉት የቦርዱ አባል የሚከተለውን አረጋግጠዋል፤<br>ሀ) አቶ ሱፍያን አህመድ የቦርዱ አባል ከመሆናቸው በተጨማሪ የገንዘብ ሚኒስትርም ናቸው። በዚህ አንፃር እርሳቸው ሳያውቁትና ሳያፀድቁት የተፈፀመ የአንድም ድርጅት ሽያጭ እንደሌለ አረጋግጠዋል፤ /ገፅ 29/። በተለይ በጣይቱ ሆቴል ሽያጭ ላይ መንግስትም ያወቀውና እሳቸውም የፈረሙ ስለመሆኑ መስክረዋል /ገፅ 30/።<br>ለ) የጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴ " የውሳኔ ሃሳብ አቅራቢ ቴክኒካል ኮሚቴ እንጂ የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ እንዳልሆነ፤ ውሳኔ ሰጪው የስራ አመራር ቦርድ መሆኑን አስረድተዋል። በዚሁ መሰረትም የጉለሌ ሳሙና ፋብሪካ ለአቶ ፍፁምዘኣብ እንዲሸጥ የወሰነው እርሳቸውም የተሳተፉበት ቦርድ በሙሉ ድምፅ መሆኑን አረጋግጠዋል። /ከገፅ 30 እስከ 31/ ይህ አባባላቸው ገፅ 34 ላይም ግልፅ አድርገው ደግመውታል።<br>ሐ) የቦርዱ ሰብሳቢ፤ከሌሎቹ አባላት የተለየ ስልጣንም ይሁን ሃለፊነት የሌለው ስለመሆኑ፤ከሌሎች አባላት ጋር እኩል ድምፅና እኩል ተጠያቂነት ያለው መሆኑን አስረድተዋል። ከዚህ ውጭ የተደበቀ ነገር አለ ብለው እንደማይጠረጥሩና እንደማያምኑም አስረድተዋል። /ከገፅ 34 እስከ 36/ |
| 75 | አቶ መስፍን ለማ የተባሉት የዐቃቤ ህግ ምስክር መጋቢት 22 ቀን 1995 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ ከሰጡት ቃል ውስጥ በከፊል የቀረበ / 7 ገፅ/<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>/1.3.10.11.12.13.14/<br><br>A - 05 | 75. አቶ መስፍን ለማ የቦርድ አባል ከመሆናቸው በተጨማሪ የጠ/ሚ/ር ፅ/ቤት የህግ ቢሮ ሃላፊም ናቸው። በሰጡት ምስክርነት የሚከተሉትን አስረድተዋል፤<br>ሀ) በቦርዱ አባላትና በሰብሳቢው መካከል በሃላፊነትና በተጠያቂነት ደረጃ ምንም አይነት ልዩነትና መበላለጥ የለም። /ገፅ 10 እና 11/ እኩል ድምፅ እኩል ተጠያቂነት ነው ያላቸው። /ገፅ 14/<br>ለ) ፕራይቬታይዝ የሚደረጉትን ድርጅቶች የሚመርጠው መንግስት ስለመሆኑ፤በዚህ መልኩ ሪፖርት ቀርቦ ጥቅምት 20 ቀን 1990 ዓ.ም በጠ/ሚ/ር ›ፅ/ቤት፤በጠ/ሚ/ር/ መለስ ዜናዊ ሰብሳቢነት ውይይት የተደረገ መሆኑን፤ በዚህም ስብሰባ ዶ/ር ካሱ ይላላ /ም/ጠ/ሚ/ር/፤ ዶ/ር ከበደ ታደሰ፤ አቶ አሰፋ አብርሃ፤ አቶ መስፍን ለማና አቶ በሻህ አዝምቴ መሳተፋቸውን አስረድተዋል።<br>ሐ) በዚህ ስብሰባ ላይ በየዘርፉ ከነበሩት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ ፕራይቬታይዝ የሚደረጉትና በመንግስት ይዞታ ስር የሚቆዩት ተለይተው የተቀመጡ መሆኑን፤ ስብሰባው የተካሄደው አዲሱ አዋጅ ቁጥር 146/91 ከመውጣቱ በፊት መሆኑና የተያዘውን ቃለ ጉባኤም የሚያውቁት መሆኑን ለፍ/ቤቱ አረጋግጠዋል። /ከገፅ 12 እስከ 13/ |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| 76 | አቶ ጀነነው አየለ የተባሉት የዐቃቤ ህግ ምስክር የካቲት 26 ቀን1995 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ ከሰጡት ቃል ውስጥ በከፊል የቀረበ / 5 ገፅ/ የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል። /1.9.14.23.24/ A - 06 | 76. አቶ ጀነነው አየለ ቀርበው በመሰከሩበት ወቅት ካነሱዋቸው ጉዳዮች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል። ሀ) ደ/ዘይት ዱቄት ፋብሪካን ባካተቱት የመጀመሪያዎቹ የኤጀንሲው ጨረታዎች ለተጫራቾች የተገለፀ ጠቋሚ ወይም መነሻ ዋጋ የሚል አልነበራቸውም። /ገፅ 14/ ለ) የተቆጣጣሪ ባለስልጣን የሚባለውና ኤጀንሲው በመሰረቱ ስራቸው የተለያየ ስለመሆኑና በቀጥታ የሚያገናኛቸው ጉዳይ እንደሌለ፤ ፕራይቬታይዝ የሚደረጉት ድርጅቶችን ለመንግስት አቅርቦ የማስፀደቅ ጉዳይ ተቆጣጣሪ ባለስልጣንን እንደማይመለከትም አስረድተዋል፤ ከዚህ ውጭ የተቆጣጣሪው ባለስልጣን ፅ/ቤት ሃላፊና የቦርዱ ሰብሳቢ አንድ ሰው መሆኑ የመ/ቤቶቹን ግንኙነት እንደማያሳዩ መስክረዋል። /ገፅ 23 እና 24/። |
| 77 | አቶ ወ/ጊዮርጊስ ወልዱ የተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክር ህዳር 25 ቀን 1995 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ ከሰጡት ቃል በከፊል የቀረበ / 4 ገፅ/ የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል። /1፣ 56፣ 72፣ 73/ A — 07 | 77. የጉለሌ ሳሙና ፋብሪካን ጨረታ የገመገመው ኮሚቴ ሰብሳቢ የነበሩት አቶ ወ/ጊዮርጊስ፣ በጨረታው ውስጥ ለአሸናፊነት መመዘኛ ሆኖ የተቀመጠው ዋጋ ብቻ እንደነበረና በዚህ መመዘኛ አሸናፊው አቶ ፍፁምዘአብ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። ከዚህ ውጭ የአፈፃፀም ችግር እንዳያስከትል የፋብሪካውን መቶ ፐርሰንት እንገዛ ላሉት ይሸጥ የሚለው ሃሳብ በጨረታው መመሪያ ውስጥ በመመዘኛነት ያልተቀመጠ ጉዳይ መሆኑንም አስረድተዋል። የኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ የመጨረሻ ውሳኔ አለመሆኑንም መስክረዋል። / ገፅ 72 እና 73/ |
| 78 | አቶ ደመቀ ሶሪ የተባሉት የዐቃቤ ሕግ ምስክር የካቲት 7 ቀን 1995 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ ከሰጡት ቃል በከፊ የቀረበ። / 10 ገፅ / የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል። /1፣ 40፣ 46፣ 47፣ 49፣ 50፣ 51፣ 52፣ 53 ፣ 54/ A - 08 | 78. ምስክሩ ከሰጡት ቃል ውስጥ የሚከተለውን መረዳት ይቻላል። ሀ) ለጉለሌ ሳሙና ፋብሪካ ከቀረቡት ተጫራቾች መካከል የአቶ ፍፁምዘአብ ዋጋ ከፍተኛ መሆኑን፣ ንፅፅሩ የተደረገው የሁለቱንም ተወዳዳሪዎች ወደ አንድ አይነት አሀዝ በመቀየር መሆኑና፣ የውሳኔ ሀሳቦችን መርምሮ ከመንግስት ጋር ተመካክሮ በመጨረሻ ላይ ውሳኔ የሰጠው ቦርዱ መሆኑን። /ገፅ 46፣47/ ለ) የደብረ ዘይት ዱቄት ፋብሪካ ላይ የተሠራው ተመን ማነፃፀሪያ አሀዝን እንጂ ዋጋን እንደማይወስን፤ ዋጋ የሚወሠነው በገበያ ሲሆን ኤጀንሲው የሚሠራው ግን ለማነፃፀሪያ የሚሆነው ጠቋሚ አሀዝ መሆኑን። /ገፅ 49/ የደብረ ዘይት ዱቄት ፋብሪካ ሽያጭ በመጨረሻ የተወሰነው እና ተፈፃሚ የሆነው የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በሰጠው ውሳኔ መሆኑን። /ገፅ 50/ ሐ) የሽያጭ ዋጋ የሚወሠነው ኤጀንሲው ባቀረበው ተመን ብቻ ሰይሆን ሌሎች ሁኔታዎችንም ባገናዘበ መልኩ ስለሚሆን ከተመኑ ዝቅ ተብሎም መሸጥ የሚቻልና የተለመደ መሆኑን። / ከገፅ 51- 54/ |
| 79 | አቶ ፀጋዬ መካሻ የተባሉት | 79. አቶ ፀጋዬ መካሻ የኤጀንሲው የህግ አማካሪ ሆነው የሠሩና የሽያጭ ውሎችን አዘጋጅተው |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | የዐቃቤ ሕግ ምስክር ጥር 1 ቀን 1995 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ ከሰጡት ቃል ውስጥ በከፊል የቀረበ። / 21 ገፅ /<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>/1፣2፣7፣8፣9፣13፣14፣ 15፣24፣25፣29፣31፣ 32፣35፣36፣37፣38፣ 39፣44፣45፣51፣/<br><br>A - 09 | ያፈራረሙ ናቸው። በዚህ አንፃር ከሰጡት ምስክርነት ውስጥ የሚከተለውን እንረዳለን።<br>ሀ) የጨረታ ገምጋሚ ኮሚቴ አባል ሆነው የጉለሌ ሳሙና ፋብሪካን ጨረታ ሲገመግሙ፣ በዋጋ አሸናፊ የሆኑት አቶ ፍፁምዘአብ መሆናቸውን እንደሚያውቁ፣ ማነፃፀሪያውም በመመሪያው መሠረት ዋጋ እንደነበረ። /ገፅ ከ7-9/<br>ለ) የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ እንዲሸጥ የመጨረሻ ትዕዛዝ የሰጠው የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እንደሆነና እሳቸውም ውሉን አዘጋጅተው ሽያጩን ያፈራረሙት ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የተላከውን የጽሁፍ መመሪያ መሠረት አድርገው እንደነበረ። /ገፅ 13/ ከዚህ ውጭ ጨረታው ከተከፈተ በኋላ የቀረበ የዋጋ ለውጥም ይሁን ድርድር አልነበረም /ገፅ 14/፣ በወቅቱ በነበረው አሠራር የቦርዱ ውሳኔ ተፈጻሚ የሚሆነው የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ሲያፀድቀው ብቻ እንደነበረና ይኸም ከአዋጁ ጋር የሚቃረን አሠራር መሆኑን። /ገጽ15/<br>ሐ) በደብረ ዘይት ዱቄት ፋብሪካ የጨረታ ሰነድ ላይ የተገለጸ መነሻ /ጠቋሚ ዋጋ አልነበረም፣ ማነፃፀሪያ ዋጋው ቦርዱ ተምኖ ለኮሚቴው የነገረው እንጂ ለተጫራቾች አልተገለጸም ነበር። /ገጽ 24/<br>መ) የመጨረሻ ውሳኔ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እየቀረበ የማስወሰኑ አሰራር እስከ 1988 ዓ.ም ድረስ ቀጥሎ ከዚያ እንደቀመ፤ ስለሆነም ጉለሌ ሳሙና ፋብሪካንና ጣይቱ ሆቴልን እንደማይመለከት፤ ከጠቋሚ ዋጋ በታች አትሽጡ የሚል ሕግም ሆነ መመሪ የሌለ መሆኑን። /ገጽ 25/<br>ሠ) ኤጀንሲው ሥራውን ሲጀምር ከመንግስት በኩል ከፍተኛ ጫና እና ጥድፊያ የነበረው መሆኑን። /ገፅ 26/<br>ረ) የጨረታ ኮሚቴ ሃሳብ አቅራቢ እንጂ ወሳኝ አይደለም፣ ወሳኞቹ የሥራ አመራር ቦርድና የጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት ናቸው። /ገፅ 29/<br>ሰ) በሐረር ማተሚያ ቤት ላይ ተጫራቹ አሸናፊነታቸው በተገለፀላቸው 10 ቀን ባልሞላ ጊዜ 40 ፐርሰንት የከፈሉ መሆኑን፤/ገጽ 31 እና 32/<br>ሸ) በጉለሌ ሳሙና ፋብሪካ ሽያጭ ላይ ቦርዱ የሰጠው ውሳኔ፣ የመንግስትን ጥቅም ያስጠበቀና በአፈጻጸም ላይ ይከሰታል በሚል የጨረታ ኮሚቴው የጠቀሰው ስጋትንም ያስወገደ እንደነበረ፤ /ገጽ 35 እና 36/ የአቶ ፍፁምዘአብ ግዢ ከ51 ፐርሰንት ወደ 100 ፐርሰንት ከፍ ያለው በቦርዱ ውሳኔ መሰረት፤ ተጠይቀው በሰጡት መልስ እንጂ ገዢ በጠየቁት መሰረት አለመሆኑን። /ገፅ 39/<br>ቀ) የደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ጨረታ ተዘግቶ፤ ከዚያም ተጫራቾች በተገኙበት ተከፍቶና በኮሚቴ ተገምግሞ የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ውሳኔ የሰጠበትን ሂደት በዝርዝር ካስረዱ በኋላ የጠ/ሚ/ር ጽ/ቤት ውሳኔውን የሰጠው ይህን ፋብሪካ ጨምሮ በሌሎችም ድርጅቶች እንደሆነ፤ ከጠቋሚ ዋጋ በታች የተሸጠው ደግሞ ደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ብዙ ድርጅቶችም እንደነበሩ አስረድተዋል። /ገጽ 36-39/<br>በ) ኤጀንሲው ሥራውን ሲጀምር ከመንግስት በኩል፣ ከIMF እና ከዓለም ባንክ ከፍተኛ ጫናና ጥድፊያ እንደነበረበት፣ በዚህም የጨረታ ሰነድ ሳይዘጋጅ ሁሉ ጨረታ ይወጣ እንደነበረ አስረድተዋል። /ገጽ 44 እና 45/ |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| 80 | የፌደራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 68/1989 የካቲት 27 ቀን 1989 የታተመ / 7 ገፅ /<br><br>ፎቶ ኮፒ ቀርቧል።<br><br>A - 10 | 80. ይኸ አዋጅ የዋናው ኦዲተር መ/ቤትን ያቋቋመውና ምሥክር ሆነው የቀረቡት የዋናው ኦዲተር ሰራተኞችም ላቀረቡት ሪፖርት መሠረት የሆናቸው፤ ሥራውን እንዲሰሩ ስልጣኑ የሰጣቸው፤ ለሪፖርቱ ዝግጅትና ለምርመራው አካሄድም መመሪያ የሆናቸው ለመሆኑ የጠቀሱት አዋጅ ነው። እነሱ እንደዚያ ቢሉም ያቀረቡት ሪፖርት ግን ይኸ አዋጅ ያስቀመጣቸውን መርሆዎችና ድንጋጌዎችን በመፃረር የተዘጋጀ ስለመሆኑ እንደሚከተለው ያስረዳል።<br>ሀ) የመሥሪያ ቤቱ ዓላማዎች በሚለው አንቀፅ 4/2/ ላይ፤" የፌደራል መንግስትን ገንዘብና ንብረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወጡት ህጎችና ደንቦች መሠረት መሰብሰቡን፤መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ " ዋነኛ ዓላማው ስለመሆኑ ተደንግጓል። ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለው ኦዲተሮቹ ለሚያቀርቡት አስተያየትም ሆነ ሪፖርት መሠረታቸው ሊሆን የሚገባው በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጸደቁና በነጋሪት ጋዜጣ የታወጁ ህጎችና ደንቦች ብቻ ናቸው። ከዚህ ውጭ በግለሰቦች አስተያየትና የመ/ቤቶች የውስጥ መመሪያ መሠረት አስተያየትም ይሁን ሪፖርት ማቅረብ አይችሉም። ከዚህ በተጨማሪ ሪፖርት የሚያደርጉት ለሌላ ማንኛውም አካል ሣይሆን ለም/ቤቱ ብቻ ስለመሆኑ ግልፅ ነው። ሪፖርት አቀራረብን በተመለከተ በተለይ በአንቀፅ 7/5/ ላይ "ያከናወነው የምርመራ ውጤት እነደነገሩ ሁኔታ ለፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቱ እና ለድርጀቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፡… ወንጀል መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ከሆነ ወዲያውኑ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሪፖርት ያደርጋል" ይላል። በተመሣሣይ መልኩ በአንቀፅ 13 ላይ ደግሞ "… ኦዲት ሲያከናውን በጉዳዩ ላይ ወንጀል መሠራቱን ያመነ እንደሆነ ይህንኑ ለፍትህ ሚኒስቴርና ለሚመለከቱት ኦዲት ተዳራጊ መ/ቤት ወይም ድርጅት የበላይ ሃላፊ ማስታወቅ አለበት" ይላል።<br>ለ) ከፍ ብለው ከተደነገጉት አንፃር ለዚህ ፍ/ቤት በማስረጃነት የቀረበው ሪፖርት መሠረት ያደረገው የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ መመሪያዎች፣ የሰዎች አስተያየትና መጠይቆች በመሆናቸው፣ አዋጁ ተጥሷል። ሪፖርቱ ተዘጋጅቶ ለፍ/ቤት መቅረብ ከነበረበት እንኳን መጀመሪያ ጉዳዩ ለሚመለከተው የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲና ለአመራሩ፣ ከዚያም ለተወካዮች ም/ቤትና ለፍትህ ሚኒስቴር ቀርቦ ከታየና ከተመረመረ፤ ወንጀል ስለመሠራቱ ከተረጋገጠ በኋላ ነበረ። ይህ ሪፖርት በዚህ ሁሉ ሂደት ሣያልፍና በቀጥታ ለፍ/ቤት የቀረበ ለመሆኑ ኦዲተሮቹም መስክረዋል።<br>ሐ) ዋናው ኦዲተር ተጠሪነቱ በቀጥታ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ስለመሆኑ በአንቀፅ 5/2/ እንደዚሁም የመ/ቤቱ በጀት የሚፀድቀው በቀጥታ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ቀርቦ ስለመሆኑ በአንቀጽ 8/5/ ተደንግጓል። በራሱ የሥራ ፕሮግራምና የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በፈቀደለት በጀት ብቻ እንዲንቀሳቀስ የተፈለገው፣ ኦዲተሩ ከሌላ አካል በተለይም ዋነኛ ተመርማሪ ከሆነው የአስፈፃሚው የመንግስት አካል ተፅእኖ ነፃ በሆነ ሁኔታ ሥራውን እንዲያከናውን ነው። ይህ ሁኔታ በተለይ በአንቀፅ 10/1/ በተደነገገው ላይ ግልፅ ሆኗል። ህጉ እንደዚህ ቢልም ይኼ አሁን የቀረበው ሪፖርት ግን በከሳሽ ወጪ፣ የሥራ መመሪያና ክትትል የተሠራ ስለመሆኑ ኦዲተሮቹም አምነዋል፤ ማስረጃም ቀርቦበታል። በዚህም ሪፖርቱ ህገ ወጥ ነው።<br>መ) ዋናው ኦዲተር የሚያደርጋቸው ምርመራዎች የሂሳብ ምርመራ፣ የክዋኔ ምርመራ የሚባሉት ብቻ ስለመሆናቸው በአንቀፅ 7/1/ እና በ7/4/ ላይ ተደንግጓል። ይሁን እንጂ ለዚህ ፍ/ቤት |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | | የቀረበው ሪፖርት "ልዩ ኦዲት ሪፖርት" የሚል ነው፤ በዚህም ህገወጥ ነው። በህግ ያልተፈቀደለትን ሥራ ነውና የሠራው።<br>ሠ) አዋጁ ዋናው ኦዲተር የሚያካሄዳቸው ምርመራዎች ስለሚመሩበት ስርኣትም በአንቀፅ 11 ላይ ደንግጓል። አንቀፅ 11/1/ በሚያዘው መሠረት ኦዲት መደረግ የነበረበት አንድ በአንድ በዝርዝር ማለትም ኤጀንሲው ፕራይቬታይዝ ያደረጋቸውን ከ200 በላይ የሚሆኑ ድርጅቶች በሙሉ፣ ካልሆነ ደግሞ በአልፎ አልፎ የኦዲት ዘዴ ማለትም ፕራይቨታይዝ ከተደረጉት ውስጥ በታወቀ መስፈርት መሠረት ናሙና ተወስዶ መሆን ሲገባው፣ አሁን ኦዲት የተደረገው ግን ከሳሽ መርጦ በሰጠው 5 ድርጅቶች ላይ ብቻ ያነጣጠረ ነው። በዚህም ሪፖርቱ ህገ ወጥ ነው።<br>ረ) በአንቀፅ 11/2/ እንደተደነገገው ኦዲቱ መደረግ የነበረበት ከሚመረመረው የበጀት ዓመት ማለትም ከ1993 ዓ.ም ወደኋላ ከሁለት የበጀት ዓመት ማለፍ አልነበረበትም። ከዚህ በኋላ አልፎ ለመመርመር ከፈለገ ወንጀል ስለመሠራቱ ማመን አለበት፣ ከዚያም በኋላ በአንቀፅ 7/5/ መሠረት ለተወካዮች ም/ቤት ሪፖርት ማድረግ አለበት። የአሁኑ ሪፖርት የተዘጋጀው ከ1993 ዓ.ም ወደኋላ በመሄድ ሳይሆን ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ወደፊት በመሄድ ነው። በዚህም ህግን ተፃርሮ የተሠራ ህገወጥ ሥራ ነው።<br>ሰ) ከፍ ብሎ በአጭሩ እንደቀረበው፣ ይሄ ሪፐርት ተዘጋጅቶ የቀረበበትና በኦዲተሮቹና በማስረጃዎቹ የተረጋገጠው ሥርዓት አዋጅ ያስቀመጣቸውን ድንጋጌዎች የጣሰ ነው። በዚህም ሪፖርቱ ህገ ወጥ እንደመሆኑ በእኔ ላይ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብብኝ አይገባም። |
| 81 | የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮምሽን ሰኔ 13/1993 ለፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የሰጠው የሥራ ትእዛዝ /1 ገፅ/<br><br>ዋናው በኮሚሽኑ ዘንድ የሚገኝ፤ ፎቶ ኮፒ ቀርቧል።<br>A - 11 | 81. የዋናው ኦዲተር ተጠሪነት ለተወካዮች ም/ቤት ብቻ መሆኑ በህግ ተደንግጎ እያለ፣ እኛን ከህግ ውጭ እና ካለምንም ማስረጃ ያሰረው አካል፣ ዋና ኦዲተሩንም " በአስቸኳይ የኦዲት ቡድኖች ተቋቁመው ..." የምርመራ ሥራ እንዲያካሄድና ውጤቱም እንዲገለፅለት ትእዛዝ ሰጥቷል። ትእዛዙ ሥልጣን ካልተሰጠው አካል የመነጨ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ኦዲት የሚደረገው በቡድኖች እንደሚሆን፣ ሪፖርቱ ደግሞ ህጉ በሚጠይቀው መስመር በኩል ሳይሆን በቀጥታ ለኮሚሽኑ እንዲላክ የሚያዝ በመሆኑ ተእዛዙም ህገ ወጥ ነው። ትእዛዙ የተሰጠው ተጠርጣሪዎች የተባሉት ከታሰሩ በኃላ ወንጀል ለማፈላለግ በተጀመረው ጥረት ለመሆኑ ደብዳቤው ራሱ ይገልፃል። |
| 82 | የፌደራል ዋና ኦዲተር ለፌደራል ስነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሰኔ 27 ቀን 1993 የሰጡት መልስ የያዘ ደብዳቤ /2 ገፅ/<br><br>ዋናው በዋና ኦዲተር መ/ቤት የሚገኝ ፎቶ ኮፒ ቀርቧል።<br>A - 12 | 82. የዋናው ኦዲተር ባጀት በተወካዮች ም/ቤት እንደሚያዝለት፣ ሠራተኞች የሚተዳደሩትም በሲቪል ሰርቪስ ደንብ መሠረት ስለመሆኑ በህግ ተደንግጎ እያለ፣ ዋናው ኦዲተር የሥራ ትእዛዝ ከኮሚሽነሯ ከተቀበሉ በኋላ የበጀት ጥያቄያቸውን ለኮሚሽነሯ አቅርበዋል። ከደብዳቤው መረዳት እንሚቻለው፣ ለመደበኛው ሥራ የማይሰጥ፣ የትራንስፖርት አገልግሎት፣ በከተማ ውስጥ የምሳ አበል እንደዚሁም የሞባይል ስልክ፤ ለኦዲተሮቹ እንዲሰጣቸውም ጠይቀዋል። የዚህ አይነት ልዩ ጥቅማ ጥቅም ከዚህ ጊዜ ውጭ ተሰጥቶአቸው እንደማያቅ ኦዲተሮቹም ለፍ/ቤት አስረድተዋል። በዚህም የሙያ ነፃነታቸውና ገለልተኛነታቸው ጥያቄ ውስጥ እንደገባ ግልፅ ነው። |
| 83 | ወ/ሮ ዝናሽ ከፍአለ | 83. ወ/ሮ ዝናሽ ከፍአለ፣ ለዚህ ፍ/ቤት የቀረበውን ሪፖርት በቡድን መሪነት አዘጋጅተው የላኩት |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | የተባሉት የዋናው ኦዲተር ሰራተኛ መስከረም 21 ቀን እና 25 ቀን 1996 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ ከሰጡት ቃል በከፊል የቀረበ / 18 ገፅ/<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>/1፣12፣15፣16፣19፣27፣42፣ 43፣49፣51፣52፣53፣54፣59፣62፣119፣120፣169 /<br><br>A - 13 | ሲሆኑ፣ በዚህ የምስክርነት ቃላቸው፤<br>ሀ) ለዚህ ሥራ የወጣው በጀት ከመደበኛ ውጪ የሆነ እንደነበረ፣ በዚህም ልዩ ኦዲት እንደተባለ፣ ትክክለኛው የኦዲት አይነት ግን የክዋኔ ኦዲት የሚባለው እንደሆነ ተናግረዋል። ይሁን እንጂ የመሥሪያ ቤታቸውን የክዋኔ ኦዲት መመሪያ በሚያዘው መሠረት ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት አስተያየት ሳይሰጡበት ለፍ/ቤት መቅረቡ መመሪያውን እንደሚፃረርና አግባብ እንዳልሆነ አስረድተዋል።<br>ለ) ለፍ/ቤቱ ያቀረቡትን ሪፖርቶች እነዲያረጋግጡ ተጠይቀውም አልቻሉም።<br>ሐ) በቡድኑ ውስጥ አንድም የተረጋገጠለት ኦዲተር እንዳልነበረ መስክረዋል።<br>መ) በሪፖርቱ ላይ "ይጠየቁበታ" በሚል የተገለፀው፣ ሃላፊነት አለባቸው ወይም ይከሰሱ ለማለት ሳይሆን፣ ማብራሪያ ይስጡበት ለማለት እንደሆነ አስረድተዋል።<br>ሠ) ኦዲቱ፤ ህግ በሚያዘው ስርዓት መሠረት አለመካሄዱን አምነው ምክንያቱ ግን ኮሚሽኑ በዚህ መልኩ እንዲሠራለት ስለጠየቀ መሆኑ አስረድተዋል።<br>ረ) በሪፖርቱ መግቢያና ማጠቃለያ ላይ የተቀመጡት አስተያየቶች የእርሳቸው እንዳልሆኑ፤ ይኸን በሚመለከት መልስ መስጠት እንደማይችሉ አረጋግጠዋል።<br>ሰ) ድርጅቶቹ ፕራይቬታይዝ እንዲደረጉ የተወሰነበት ማስረጃ ይቅረብ ያሉት አዋጅ ቁጥር 146/91 መሠረት አድርገው እንደሆነ፤ ይኸ አዋጅ ወደ ኋላ ተመልሶ እንዴት ተፈፃሚ እንደሚሆን ግን ያላስተዋሉት ጉዳይ መሆኑን፤<br>ሸ) አባሪ አድርገው ከሪፖርቱ ጋር ያያዟቸው ሠንጠረዦች እንደነበሩ ይዘታቸውም በአብዛኛው በውሣኔ አሰጣጡ ሂደት የተሳተፉትን የቦርድ አባላት የሚዘግብ መሆኑን፤<br>ቀ) ሞባይል ስልክ፤ አበልና የመሣሠሉት ጥቅማ ጥቅሞች ይኸን ሥራ ሲሰሩ እንጂ ከዚያ በፊትም ሆነ በኋላ ተሰጥቷቸው እንደማያውቅ፤ አስረድተዋል። |
| 84 | አቶ አለማየሁ ግርማ፣ የተባሉ የዋናው ኦዲተር መ/ቤት ሠራተኛ መስከረም 27 ቀን 1996 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ ከሰጡት ቃል ውስጥ በከፊል የቀረበ<br>/ 16 ገፅ /<br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br>/1፣3፣6፣22፣23፣27፣28፣37፣38፣42፣43፣45፣46፣47፣48፣84 /<br>A - 14 | 84. እኚህ ምስክር፣ በልዩ ሁኔታና በተለየ አበል የተሠራ ኦዲት ስለመሆኑ፣ እሳቸውም ይህን ሥራ ሲሰሩ የ12ኛ ክፍል ተማሪ እንደነበሩ፣ በአጠቃላይ ሥራውን ከሰሩት ውስጥ አንድም የተመሰከረለት ኦዲተር እንደሌለ አረጋግጠዋል። እሳቸው በሪፖርቱ ላይ እንዳልፈረሙ፣ ሪፖርቱ ተፅፎ ወጪ የተደረገው በአለቆቻቸው በኩል እንደሆነ ይኸ ሪፖርት በቡድን መሪ ተፅፎ፣ "ሌሎች ሰዎች" ያሏቸው ደግሞ አስተያየት ጨምረውበት በዋናው ኦዲተር ሽኚነት የተላከ መሆኑን አስረድተዋል። የኦዲቱ ዓይነት የክዋኔ ኦዲት እንደሚባል፤ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰዎች አስተያየት እንዳልሰጡበት ነገር ግን ሊሰጡበት ይገባ እንደነበረ፤ ሪፖርቱ በኮሚሽኑ ትእዛዝ በአምስቱ ድርጅቶች ብቻ ማተኮሩ፤ ነፃ ቢሆኑ ግን ኤጀንሲው ከሸጣቸው ድርጅቶች ውስጥ ናሙና በመውሰድ ይሠሩት እንደነበረ አስረድተዋል። በደብረዘይት ዱቄት ፋብሪካ ጨረታ ላይ የተገለፀ ጠቋሚ ዋጋ እንዳልነበረም አስረድተዋል። |
| | | |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| 85 | አቶ አገርነህ ጌታሁን የተባሉ የዋናው ኦዲተር መ/ቤት ሠራተኛ ጥቅምት 10 ቀን 1996 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ ከሰጡት ቃል ውስጥ በከፊል የቀረበ / 12 ገፅ /<br><br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል። /1፣22፣23፣31፣32፣33፣34፣<br>39፣40፣41፣81፣82 /<br>A - 15 | 85. ምስክሩ ልዩ አበል እየተከፈላቸው ፣ በኤጀንሲው ፅ/ቤትና ፀሐፊ ተመድቦላቸው፣ መኪና ከነሹፌሩና ሞባይል ስልክ ተሰጥቷቸው፣ የሰሩት ልዩ ኦዲት ስለመሆኑ አስረድተዋል። የኦዲቱ አይነት የክዋኔ ኦዲት ወይም (performance audit) የሚባል እንደሆነ ቢገልፁም፣ የመ/ቤቱ የክዋኔ ኦዲት መመሪያ መሠረት አድርጎ ያልተሰራ መሆኑን አረጋግጠዋል። በተለይም ሪፖርቱ ለተመርማሪ መ/ቤትና ለሚመለከታቸው ሰዎች ተልኮ የነሱን አስተያየት ማካተት እንደነበረበት፣ ለተወካዮች ም/ቤትም መቅረብ እንደነበረበት አምነዋል። ከዚህ በተጨማሪ ኦዲቱ መሠራት የነበረበት በሙያው ማረጋገጫ በተሰጣቸው ሰዎች እንደሆነ፣ ይሁን እንጂ ባለሙያ ስለጠፋ በልምድ እንደሰሩት መስክረዋል። በቡድኑ ውስጥ አንድም የተመሠከረለት የሂሳብ ባለሙያ እንዳልነበረ፤ እንደውም አቶ ዓለማየሁ ግርማ የተባሉት የ12ኛ ክፍል ተማሪ እንደሆኑ፤ አረጋግጠዋል። ከዚህ በተጨማሪ የኤጀንሲው የሥራ መመሪያ የወጣው በ1989 ዓ.ም እንደመሆኑ፤ ከዚያ በፊት ለተሠሩት ሥራዎች መሠረት ሊሆን እንደማይችል አስረድተዋል። |
| 86 | አቶ ጌታቸው ተክሉ የተባለ የዋናው ኦዲተር መ/ቤት ሠራተኛ ጥቅምት 19/1996 ዓ.ም ለፍ/ቤቱ ከሰጡት ቃል ውስጥ በከፊል የቀረበ / 5 ገፅ/<br>የኤጀንሲው ማህተም ያረፈበት ዋና ኮፒ ተከሳሾች ዘንድ ይገኛል፤ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል። /1፣2፣5፣33፣34 /<br>A - 16 | 86. ምስክሩ ይህን ሥራ በሰሩበት ወቅት ዲግሪም ሆነ ሌላ የሙያ ማረጋገጫ እንዳልነበራቸው ፤ አሠራሩ ከመ/ቤቱ አሠራር የተለየ፤ የኦዲቱ ስም ግን ፐርፎርማንስ አዲት እንደሆነ መስክረዋል። |
| 87 | የዋናው ኦዲተር መ/ቤት የክዋኔ ኦዲት ማንዋል፣ በከፊል የቀረበ /6 ገፅ/<br><br>ዋናው በተከሳሾች እጅ ይገኛል፣ ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>/ 1፣20፣21፣138፤139፤140 /<br><br>A - 17 | 87. የቀረበው ሪፖርት ምን ዓይነት እንደሆነ፣ ኦዲተሮቹ ተጠይቀው የሰጡት መልስ የክዋኔ ኦዲት የሚባል እንደሆነ አስረድተዋል። ምስክሮቹ የክዋኔ ኦዲት ብለው የጠሩት ሪፖርት የተዘጋጀው በመ/ቤቱ መመሪያ መሠረት እንደሆነ ለማስመሰል ሞክረው ሪፖርቱን መሠረት አድርገን ስንጠይቃቸው፣ በመመሪያው መሠረት አለመሠራቱን አምነዋል። ከዚህ በተጨማሪ ይኸ የክዋኔ ኦዲት መመሪያ ወይም (performance audit manual) የሚከተሉትን ያስረዳል።<br>ሀ) የክዋኔ ኦዲት ዋነኛ ትኩረት በእኛ ላይ እንደተደረገው ሰዎችን አስሮ ጥፋት ለማግኘት ሳይሆን የተሻለ አሠራር ለመፍጠር እገዛ ለማድረግ መሆኑ /ገፅ 1/<br>ለ) ግቡን ለማሳካት ኦዲተሮችም ሆነ መ/ቤቱ ሙያዊ ነፃነታቸውን መጠበቅ እንደሚገባቸው፣ በተለይም ከማንኛውም የገንዘብና የጥቅም ተፅዕኖ ነፃ መሆን፣ ምርመራ የሚያካሄዱበትን የሥራ ዘርፍና የምርመራውን ስርዓት የመምረጥ ነፃነት፣ ሪፖርታቸውን ነፃ በሆነ ስሜትና ከተፅዕኖ ውጭ አዘጋጅተው ጉዳዩ ለሚመለከታቸው በግልፅ ሪፖርት ማድረግ፣ እንደሚገባ ተደንግጓል /ገፅ 20 እና 21/<br>ሐ) የሪፖርቱ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለተመርማሪው መ/ቤት መላክ እንዳለበት፣ ከዚያም ከሃላፊዎቹና |

| ተ.ቁ | የሰነዱ መጠሪያ፤ የገፅ ብዛትና መለያ ኮድ | ሰነዱ የሚያስረዳቸው ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች |
|---|---|---|
| | | ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሰዎች ጋር የጋራ ውይይት ማድረግ የግድ እንዳለበት፣ የተመርማሪዎች ሃሳብ በሪፖርቱ ማካተት እንዳለባቸው መመሪያውም ያዛል። /ገፅ 138/ አዋጁ፣ መመሪያውና ያዘጋጁት ምስክሮች እንዲህ በግልጽ ህገ ወጥነቱን የመሰከሩበት ሪፖርት ማስረጃ ሆኖ ለዚህ ፍ/ቤት ሊቀርብ እንደሚይገባውና እኔን ለማስቀጣት ብቃቱ የሌለው ለመሆኑ ገልፅ ሆኗል። |
| 88 | ሐምሌ 2 ቀን 1998 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ በከፊል የቀረበው ኮፒ .4 ገፅ<br><br>ፎቶ ኮፒ ቀርቧል።<br><br>A - 18 | 88. ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሰኔ 27 ቀን 1998 ለተወካዮች ም/ቤት ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት ከተነሱት በርካታ ጉዳዮች ውስጥ በርካታ የመንግስት ገንዘብ የጎደለ በመሆኑ የሚዘግበውና ቀደም ባሉት ሳምንታት ለተወካዮች ም/ቤት ቀርቦ የነበረው የዋናው ኦዲተር ዐመታዊ ሪፖርት አንዱ ነበር። ይህ የዋናው ኦዲተር ሪፖርት ከተዘጋጀ በኋላ ለተመርማሪ መ/ቤቶች ሳይላክና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶችና ኃላፊዎች ጋር ውይይት ሳይደረግበት በቀጥታ ለተወካዮች ም/ቤት የተላከ መሆኑን ካስረዱ በኋላ፤ ሪፖርቱ የኦዲት ስነምግባርን ተከትሎ ያልተሰራ ነው ብለውታል። ስለሆነም ጉድለት ተብለው በሪፖርቱ የተጠቀሱት ጉዳዮች ተቀባይነት የሌላቸው ስለመሆኑ ለፓርላማው አረጋግጠውለታል። ይኸ አባባላቸው እኔ ለዚህ ፍ/ቤት እያቀረብኩ ካለሁት ክርክር ጋር የተጣጣመና የክርክሬንም ሀቀኝነት ያረጋገጠልኝ ነው። |
| 89 | መስከረም 4 ቀን 1999 ዓ.ም ከፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ፤ የዋናው ኦዲተር መ/ቤት ያዘጋጀውን ሪፖርት በሚመለከት የተሰጠ ማረጋገጫ፤ / 1 ገፅ /<br><br>ዋናው በተከሳሾች እጅ ይገኛል ፎቶ ኮፒው ቀርቧል።<br><br>A - 19 | 89. ቀደም ሲል የመንግሥት የልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣንና የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በሚል ይታወቁ የነበሩት ሁለት የተለያዩ አካላት ከሐምሌ 26 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ በአዋጅ ቁጥር 412 /1996 መሠረት ተዋህደው አንድ አካል ሆነዋል።<br>ይህ የአሁኑ መ/ቤት ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 87/1986 እና በአዋጅ ቁጥር 146/1991 መሠረት የፕራይቬታይዜሽን ፕሮግራሙን ሲመራ የነበረውን የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ፤ እንደዚሁም በአዋጅ ቁጥር 25/1984 መሠረት የተሰየመውን የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣንና ፅ/ቤቱን ያዋሃደ መ/ቤት ነው። የፌደራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት ምርመራውን አዋጅ ቁጥር 68/1989 በሚያዘው መሠረት ቢያከናውን ኖሮ፤ ሪፖርቱ መጀመሪያ ከሚላክላቸውና አስተያየታቸውም እንዲሰጡበት ከሚጠየቁት አካላት መካከል ተቀዳሚዎቹ ኤጀንሲውና ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ይሆኑ ነበር። ይሁን እንጂ ሪፖርቱ ለእነዚህ አካላት ስለአለመላኩ እና የእነሱን አስተያየትም ስለአለማካተቱ ኦዲተሮቹም ያረጋገጡት ሆኖ፤ መ/ቤቱም በፅሁፍ አረጋግጦታል። በዚህም የቀረበው ሪፖርት ህገወጥ ከመሆኑ በተጨማሪ ጉድለት ብሎ የጠቀሳቸውም ተቀባይነት የሌላቸው ስለመሆኑ ያረጋግጣል። |

<u>ማመልከቻ፤</u>

1. ፍ/ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ መሠረት መግለጫና የማስረጃ ዝርዝራችንን አቅርበናል። ካቀረብናቸው ማስረጃዎች ውስጥ በተለይ በተራ ቁጥር 71 ላይ የተጠቀሰው የባለሙያዎች ሪፖርት ገና በዝግጅት ላይ ያለና በአጭር ጊዜ የሚጠናቀቅ ነው። ሪፖርቱ ተጠናቅቆ እንደደረሰን፤

ስለባለሙያ ምሥክሮቹም ሆነ ስለ ሪፖርታቸው የተሟላ መግለጫ እንድናቀርብ፣ ምሥክሮችንም አቅርበን ስለምርመራ ውጤታቸው እንዲያስረዱ እንድናደርግ ፍ/ቤቱ እንዲፈቅድልን እናመለክታለን።

2. ከተጠቀሰው ሪፖርት ውጭ ያሉትን ሰነዶቻችን በሙሉ አሟልተን ይዘን ቀርበናል። ምሥክሮቻችንም ዝግጁ ናቸው። የመከላከል ሂደቱ ቶሎ አልቆ ፍትሕ የምናገኝበትን ዕድል ለማፋጠን እንዲያስችል፤ ምሥክሮቻችን ማሰማት እንድንጀምር ትእዛዝ እንዲሰጥልን በማክበር እናመለክታለን።

<u>**አመልካቾች**</u>

1ኛ ተከሳሽ አሰፋ አብርሃ ሐጎስ የ1ኛ ተከሳሽ ጠበቃ

..................................................

............................................